


# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

## የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# በስኳር ኮርፖሬሽን የተንዳሆ ነባር ስኳር ፋብሪካ የማስፋፊያ ሥራ አፈፃፀምና ውጤታማነት ላይ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

**ጥር 2009 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

ማውጫ


የኦዲት ግኝቶች ማጠቃለያ/ Executive Summary/ .......... IV

ክፍል አንድ .......... 1

መግቢያ .......... 1

የስኳር ኮርፖሬሽን ራዕይ እና ተልዕኮ .......... 3

የስኳር ኮርፖሬሽኑ ዓላማዎች .......... 3

የኮርፖሬሽኑ መብትና ግደታዎች .......... 4

የነባር ስኳር ፋብሪካዎች የማስፋፊያ ሥራዎች ተቋራጮች ኃላፊነት .......... 4

በነባር ስኳር ፋብሪካዎች የማስፋፍያ ሥራዎች .......... 5

ከአማካሪ መሀንዲሶች የሚጠበቁ ተግባራት .......... 5

የስኳር ኮርፖሬሽን ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ሃይል .......... 5

የስኳር ኮርፖሬሽን የፋይናንስ ምንጭ .......... 6

የኦዲቱ ዓላማ .......... 6

የኦዲቱ አካባቢ .......... 6

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች እና መመዘኛ መስፈርቶች፡- .......... 7

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት እና የተዘጋጀባቸው ማስረጃዎች፡- .......... 7

የኦዲቱወሰንናዘዴ .......... 8

ክፍል ሁለት .......... 9

**ግኝቶች** .......... 9

ለስኳር ፋብሪካ ግንባታና ተከላ የጨረታ .......... 9

ሂደትና ድርድር መደረጉን በተመለከተ .......... 9

ለሸንኮራ አገዳ ተክል ልማት የመሬት ርክክብ መፈፀሙን እና የማሽነሪ .......... 10

አቅርቦት በማሟላት የመሬት ዝግጅት መደረጉን በተመለከተ .......... 10

የስኳር ፋብሪካ ግንባታ እና ተከላ ዲዛይን ቁጥጥርና .......... 14

ክትትል እና ግምገማን በተመለከተ .......... 14

የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ በታቀደለት ጊዜና በተመደበለት .......... 17

ወጪ መጠናቀቁን በተመለከተ .......... 17

ለመሬት ዝግጅትና ለሸንኮራ አገዳ ልማት የሚያስፈልጉ ግብዓትና .......... 20

አቅርቦት መሟላታቸውን በተለመከተ .......... 20

ዘመናዊ የማሽነሪዎች ጥገና እና እድሳት .......... 21

አገልግሎት መተግበሩን በተመለከተ .......... 21

በዴት ባህሪ ጋራዥ ቆመው የሚገኙ .......... 22

በቴክኖሎጂ በመደገፍ የሸንኮራ አገዳ ልማት .......... 24

ምርታማነት መሻሻሉን በተመለከተ .......... 24

ግዥዎች ግልፅነትና ተጠያቂነት ባለበት ሁኔታ ........ 25
የሚፈፀሙ መሆኑን በተመለከተ ........ 25
ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ቋሚ ንብረቶች በኮርፖሬሽኑ ........ 26
መመሪያ መሰረት የሚወገዱ መሆኑን በተመለከተ ........ 26
ምርምርና ስልጠና የተሻሻለ የሸንኮራ አገዳ እና ስኳር ........ 27
አመራረት ቴክኖሎጂን መጠቀሙን በተመለከተ ........ 27
የአካባቢ ጥበቃ እንክብካቤን በተመለከተ ........ 29
ክፍል ሶስት ........ 30
የመደምደሚያ ሀሳቦች ........ 30
ክፍል አራት ........ 32
የማሻሻያሀሳቦች ........ 32

## የኦዲት ግኝቶች ማጠቃለያ/ Executive Summary/

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 ዓ.ም በተሰጠው ስልጣን እና በኢትዮጵያ የክዋኔኦዲት ደረጃዎች መሰረት በስኳር ኮርፖሬሽን በነባር ስኳር ፋብሪካዎች የማስፋፊያ ሥራዎች አፈፃፀምና ውጤታማነት ላይ ከ 2006 በጀት ዓመት እስከ 2008 በጀት ዓመት በተከናወኑ ተግባሮች የክዋኔ ኦዲት ያከናወነ ሲሆን የኦዲቱም ዓለማ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የስኳር ኮርፖሬሽን በነባር ስኳር ፋብሪካዎች ላይ ያካሄዳቸውን የማስፋፍያ ሥራዎች አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፣ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆናቸውን መገምገም ሲሆን በተለይ ኦዲቱ በማስፋፍያ ዕቅድ የተያዙ የነባር ማስፋፍያ ሥራዎች፣የፋብሪካ ማስፋፍያ ግንባታ፣ተከላና የኮሚሽኒንግ ሥራዎች፣የመስኖ ግድብና አውታር ግንባታ ማስፋፍያ ሥራዎችን አፈፃፀም እና ከማስፋፍያ በኃላ ያለው የኦፕሬሽን አፈፃፀም ውጤታማነትን በመገምገም በአሠራር ላይ ያጋጠሙ ችግሮች ከነበሩ በመለየት ችግሮቹ የሚቀረፉበትን ወይም የሚሻሻሉበትን የማሻሻያ ሀሣቦች ለማቅረብ እና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

ኦዲቱ በስኳር ኮርፖሬሽን እና በስሩ ባለ ተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ የተከናወነ ሲሆን በኦዲቱ የተለዩት ግኝቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- EPC የተባለው ተቋራጭ እንደዋና አሰሪ ሆኖ ሌሎቹ የጨረታ አሸናፊዎች በጨረታ ውድድር ወቅት ባልተገለፀ ሁኔታ በእሱ ስር /Sub- Contractors/ ሆነው የጨረታው ዋጋ ጭማሪ በማያሳይበት/Fixed Price/ እንዲሰሩ በቀጣሪው ድርጅት የተወሰነ ሲሆን፣ ሆኖም በዋናነት እንዲመራ የተደረገው EPC ተቋራጭ እያንዳንዱ የጨረታ ተወዳዳሪ የአስተዳደር ክፍያ እንዲከፍለው በመጠየቁ ጭቅጭቅ ተነስቶ በሁለት የጨረታ ተወዳዳሪዎች ክስ በመመስረቱ ጉዳዩ ወደ ህግ የቀረረበት ሁኔታ የደረሰ ሆኖ የ EPC የኮንትራት ውል እ.ኤ.አ ጥር 2008 የተፈረመ ቢሆንም ሥራ ላይ ሊውል የቻለው ከ 18 ወራት በኋላ እ.ኤ.አ ሀምሌ 17/2009 መሆኑ፣
- በ2006 በጀት ዓመት 16,882 ሄክታር የግርድፍ መሬት ርክክብ ለመፈፀም ታቅዶ 6,953.70/41.19%/ ሄክታር ርክክብ የተፈፀመ ሆኖ 16,882 ሄክታር ውሃ ገብ መሬት ርክክብ ለመፈፀም ታቅዶ 6,434.21/38.11%/ ሄክታር ርክክብ የተፈፀመ መሆኑ፣
- የእርሻኦፕሬሽንአፈፃፀምን በተመለከተ በ 2006 በጀት ዓመት 16,882 ሄክታር መሬት ድልዳሎ ለማከናወን በእቅድ ተይዞ አፈፃፀሙ 8,251.30/48.87%/ ሄክታር መሆኑ፣
- በ2006 በጀት ዓመት 16,882 ሄክታር መሬት የኮሜርሻል/የፋብሪካ ግብዓት/ አገዳተከላለማከናወን ታቅዶ 8,220/48.69%/ ሄክታር የተተከለ መሆኑ፣

- በ2007 በጀትዓመት10,521 ሄክታር የግርድፍ መሬት ርክክብ ታቅዶ ከንውኑ 2,980/28.32%/ ሄክታር መሆኑ፣
- ውሃገብ ተብለው ወደ ፋብሪካው የሚተላለፉ መሬቶች የመስኖ አውታሮቹ የኦፍቴክ/መቀነሻ/ ችግር ያለባቸው ውሃ መሸከም የማይችሉ ሁለተኛ /ሰከንደሪ/ና ሶስተኛ /ቴሪሸሪ/ የውሃ ማሳለፊያ ቦዮች/ካናሎች/ በመገንባታቸው በቀላሉ ውሃ በሚገባ ጊዜ ካናሎቹ በውሃ የሚሸረሸሩና የሚሰበሩ መሆኑ፣
- በ2007 በጀት ዓመት 10,521 ሄክታር የኮሜርሻል አገዳ ተከላ ለማከናወን ታቅዶ የተከላው ክንውን 1316/12.51%/ ሄክታር መሆኑ፣
- የግርድፍ መሬት በውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ርክክብ ተፈፅሞ ወደ ድርጅቱ የሚተላለፍ በመሆኑ/ የመዘግየት ሁኔታ/ መኖሩ፣
- የግርድፍ መሬት አቅርቦትን በተመለከተ ፋብሪካው 22 ዶዘሮች ያሉት ሲሆን፤ 16ቱ የመለዋወጫ ችግር የገጠማቸው በመሆኑ 6ቱ ብቻ በሥራ ላይ በመዋላቸው እና ዶዘሮቹ የሰርቪስ ኪት የሚፈልጉ በመሆናቸው በግርድፍ ሥራ አቅርቦት ላይ ለዝቅተኛ አፈፃፀም አስተዋፆ ማድረጋቸው የታወቀ ሲሆን፤ እንዲሁም የውሃ ገብ መሬት 10,521 ሄክታር ለመረከብ ታቅዶ ክንውኑ 2,654/25.23%/ሄክታር መሆኑ፣
- የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ፕሮጀክትን ለማማከር በጄፒ ሙከርጂ እና በተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ የመነሻ ውል እ.ኤ.አመስከረም 2006 በመነሻዋጋዩስዲ 1,328,030 በመፈራረም ሥራው ከ እ.ኤ.አ ህዳር 22/2006 ተጀምሮ እ.ኤ.አ ሚያዚያ 23/2009 እንዲጠናቀቅ የታቀደ ቢሆንም፤ውሉ 3 ጊዜ በመራዘም ከመነሻ ኮንትራት ዋጋ ዩኤስዲ 9,474,645/713.4%/ ጭማሪ ያሳየ ሲሆን በጊዜ በኩልም ሰባት ዓመት የተራዘመ መሆኑ፣
- ለተንዳሆ የአገዳ እርሻ ልማት በመሰረታዊነት እንዲያገለግል ታስቦ የተሰራው የተንዳሆ ግድብና መስኖ ሥራ ፕሮጀክት በቀድሞው የኢትዮጵያ ውሃ ሥራዎች ድርጅት በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን የውሃ መሰረተ ልማት ኮንስትራክሽን ዘርፍ የፕሮጀክቱ ግንባታ በመስከረም ወር 1997 ዓ.ም በብር 840,254,270.70/ስምንት መቶ አርባ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሀምሳ አራት ሺህ ሁለት መቶ ሰባ ከ 70/100/ የውል ስምምነት ተፈፅሞ በ24 ወራት ጊዜ ውስጥ እንደሚጠናቀቅ ታስቦ ግንባታው የተጀመረ ሲሆን፤ በነሀሴ 2007 ዓ.ም የተጠናቀቀ ሆኖ በ 2003 ዓ.ም የውለታ ማሻሻያ ተደርጎ የኮንትራት ዋጋውም ወደ 4.15 ቢሊዮን ከፍ እንዲል የተደረገ መሆኑ፣
- የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ የአንደኛ ምዕራፍ መነሻ የኮንትራት ዋጋ ዩኤስዲ 232,820,699/ሁለት መቶ ሰላሳ ሁለት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሃያ ሺህ ስድስት መቶ ዘጠናዘጠኝ/እና ብር 589,198,859/አምስት መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ሚሊዮን አንድ መቶ ዘጠና ስምንት ሺህ ስምንት መቶ

ሃምሳ ዘጠኝ/ ፣ ሁለተኛ ምዕራፍ ዩኤስዲ 139,849,636/አንድ መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሚሊዮን ስምንት መቶ አርባ ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ ሰላሳ ስድስት/ እና ብር 269,205,899/ሁለት መቶ ስድሳ ዘጠኝ ሚሊዮን ሁለት መቶ አምስት ሺህ ስምንት መቶ ዘጠና ዘጠኝ/ ሆኖ የመነሻ ኮንትራት ውል እ.ኤ.አ ጥር 2008 ተፈርሞ በተፈጠረ አለመግባባት ምክንያት ከ 18 ወራት በኋላ እ.ኤ.አ ሐምሌ 17/2009 የተጀመረ ሆኖ የማጠናቀቂያ ጊዜ እስከ እ.ኤ.አ ሚያዚያ/2009 ቢሆንም ባለመጠናቀቁ በሚከተሉት ሁኔታዎች የኮንትራት መነሻ ዋጋ ለውጥ ሳይኖር የማጠናቀቂያ ጊዜ ማራዘሚያ የውል መሻሻያ መደረጉ ታውቋል፡፡የጊዜ ማሻሻያ ውል ያስፈለገባቸው ምክንያቶችና ውል የተደረገባቸው ቀናት እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1. እ.ኤ.አ 18/01/2010 የማሽን ተከላ ለማከናወን የሲቪል መሰረት ግንባታ ሥራዎች ለማከናወን
2. እ.ኤ.አ 18/03/2014 የስኳር ጁስ መጭመቂያ ክፍልን በሚመለከት
3. እ.ኤ.አ 18/09/2015 መለዋወጫ አቅርቦትን በተመለከተ
4. እ.ኤ.አ 22/06/ 2016 ክለሳ በማድረግ መለዋወጫ አቅርቦትን በተመለከተ /በድምር 6 ዓመት /

- በዲዛይን ለውጥ ምክንያት በውል ውስጥ የሌሉ በቁጥር 23 ተጨማሪ ሥራዎች ተሰጥተው ተቋራጩ እንዲሰራ የተደረገ መሆኑ፣
- የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ግንባታና ተከላ እ.ኤ.አ ከሐምሌ 17/2009 እስከ እ.ኤ.አ ሰኔ 2016 ድረስ የመጀመሪው ምዕራፍ 94.80% የደረሰ ሆኖ ሁለተኛው ምዕራፍ 31.39%/ ከማጠናቀቂያ ጊዜ ለ 4 ዓመት መዘግየት፤ በቤቶች ግንባታም ለ 499 ቤቶች 300 ተቋራጮች በውል ባልታሰረ ሁኔታ ሥራ የሰሩ መሆኑ፣

## ለመሬት ዝግጅትና ለአገዳ ልማት የሚያስፈልጉ ማሽነሪዎች አቅርቦት መሟላታቸውን በተለመከተ

- የቀረቡ የማሽን ዓይነቶች ብዛት 118
- በሥራ ላይ የዋሉ ማሽኖች ብዛት 54/45.76%/
- ለጥገና የገቡ ማሽኖችና መለዋወጫ ያላገኙ ብዛት 64/54.23%/ በመሆናቸው የግርድፍና የውኃ ገብ ሪክክብ፤ የመሬት ድልዳሎና የአገዳ ተከላ ልማት ዕቅዶች አፈፃፀም ላይ ተፅዕኖ ያሳደረ መሆኑ፤
- በተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ለሰራተኞች መኖሪያ የተሰሩ ብዛታቸው 499 የሆኑ ግንባታቸው ከ300 በላይ ተቋራጮች/ኮንትራክተሮች/ በኮንትራት ውል/በማስረጃነት ባልቀረበ/ መሰረት ከሀምሌ 2001 ዓ.ም ጀምሮ ብዙዎቹ በተለያየ ቀን መፈረማቸው የተገለፀ፤ እንዲሁም የሥራ ማጠናቀቂያ ጊዜያቸው

እንደ ህንፃው ዓይነት የሆነ በ 10 ወር፣በ 6 ወር፣ በ 4 ወር፣በ 3 ወር የሆነ የግንባታ ሥራውን የወሰዱት በጨረታ ስለ መሆኑ ማስረጃ የሌለ በመሆኑ ማወቅ ያልተቻለ መሆኑ፣

- ተቋራጮቹም ሆነ አማካሪ የቤቶቹን ግንባታ ለመሥራትም ሆነ የምክር አገልግሎት ለመስጠት በምን ያህል ዋጋ ሥራ እንደ ጀመሩና መቼ ለማጠናቀቅ ውል እንደ ገቡ የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ ያልተቻለ መሆኑ፣
- በ2005/2006 በጀት ዓመት በውስጥ ኦዲት ሪፖርት በተገኘ መረጃ መሰረት ከብረታብረት ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን ለማሽነሪ ብር 44 ሚሊዮን የግዥ ውል ተፈፅሞ ከውለታው ቀን በላይ አንድ ዓመት መዘግቱ፤

**ምርምርናስልጠና**

- ከ2006/07 በጀት ዓመት እቅድ አፈፃም ሪፖርት መረዳት እንደተቻለው በተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ በአገዳ እድሜ እርጅና ምክንያት የአገዳ የስኩሮዝ ይዘቱ እጅግ አነስተኛ በመሆኑ በፋብሪካው አገዳ መፍጨት ሂደት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ በማሳደሩ 1,340.9 ሄክታር የአገዳ ማሳ ሙሉ ለሙሉ የተወገደ መሆኑ፣
- የተንዳሆ እርሻ ምርምር እና ስልጠና ጣቢያ በተሰጠ ገለፃ በተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ምርት ማምረት አለመጀመር ምክንያት የቆረጣ ጊዜ ያለፈባቸው  የሸንኮራ አገዳ በ 2008 በጀት ዓመት 303.17 ሄክታር ጥቅም ላይ የማይውሉ ተብሎ እንዲገለበጥ የተደረጉ መሆኑ፣

**የአካባቢጥበቃ**

- መንደር 18 ተብሎ የሚጠራው አሳይታ የሚገኘው የአብዛኛው ሰራተኛ መኖሪያ የአካባቢውን ሞቃት ንፋስና ሙቀት መቀነስ የሚችል የዛፍ ዓይነት የማይታይበት መሆኑ በአካል ማየት መቻሉ

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

**የስኳር ኢንዱስትሪ በኢትዮጵያ**

1. ዘመናዊ የስኳር ኢንዱስትሪ በኢትዮጵያ በግል የውጭ ባለሀብቶችና በመንግስት ሽርክና በኩባንያ መልክ የተጀመረው በ 1946 ዓ.ም ከአዲስ አበባ 110 ኪሎ ሜትር ርቃ በምትገኘው ወንጂ ከተማ ላይ ሲሆን፤ በወቅቱ በሽርክና ወደ ሥራ የገባው ኤች.ቪ.ኤ የተሰኘ የሆላንድ ኩባንያ ነበር፡፡ ኩባንያው 5 ሺህ ሄክታር የሸንኮራ አገዳ ማልሚያ መሬት ተረክቦ ሰኔ 18 ቀን 1943 ዓ.ም ሥራ ጀመረ፡፡ የፋብሪካ ግንባታው መጋቢት 11 ቀን 1946 ዓ.ም ተጠናቆ ስኳር ማምረት ሲጀምር 1 ሺህ 400 ኩንታል ስኳር እያመረተምዕዙን/አንኳር/ እና ባለ አስር ሳንቲም እሽግ ስኳር ለገበያ ያቀርብ ነበር፡፡
2. በወቅቱ የወንጂ አካባቢ በዓለማችን ከፍተኛ ምርት ከሚያስመዘግቡና ለስኳር ምቹ ከሆኑ አካባቢዎች አንዱ ስለነበር ከወንጂ ስኳር ምስረታ ጋር ተያይዞ የወንጂ ከረሜላ ፋብሪካ ሰኔ 1953 ዓ.ም ተቋቁሞ ደስታ ከረሜላ እያመረተ ለገበያ ማቅረብ ጀመረ፡፡ የወንጂ ስኳር ፋብሪካ ሥራ ከጀመረ ከዘጠኝ ዓመታት በኋላ በ 1955 ዓ.ም እዛው ወንጂ ላይ የተቋቋመው የሸዋ ስኳር ፋብሪካ በወቅቱ በቀን 1ሺህ 700 ኩንታል ስኳር ያመርት ነበር፡፡
3. በ1967 ዓ.ም በተደረገው የመንግስት ለውጥ ምክንያት ስኳር ፋብሪካዎቹ በመንግስት ይዞታ ስር እንዲተዳደሩ ሆኑ፡፡ ይህን ተከትሎ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 58/1970 የተቋቋመው የኢትዮጵያ ስኳር ኮርፖሬሽን ወንጂ ሸዋና መተሐራ ስኳር ፋብሪካዎችን ጨምሮ አዲስ ከተማና አስመራ ከረሜላ ፋብሪካን እንዲያስተዳድር ተደረገ፡፡
4. የወንጂ ሸዋና የመተሐራ ስኳር ፋብሪካዎችን እንዲሁም የአዲስ ከተማንና የአስመራ ከተማን ከረሜላ ፋብሪካዎች ያስተዳድር የነበረው የኢትዮጵያ ስኳር ኮርፖሬሽን በ 1984 ዓ.ም በሕግ ሲፈርስ በምትኩ በደንብ ቁጥር 88/85 መተሐራ ስኳር ፋብሪካ፣ በደንብ ቁጥር 88/85 ወንጂ ሸዋ ስኳር ፋብሪካ እና በደንብ ቁጥር 199/86 ፊንጫአ ስኳር ፋብሪካ/በወቅቱ አዲስ የተጀመረ የስኳር ፕሮጀክት የነበረ/ እራሳቸውን የቻሉ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሆነው እንዲቋቋሙ ተደረገ፡፡
5. ይህ በእንዲህ እንዳለ ለስኳር ፋብሪካዎቹ የጋራ አገልግሎት እንዲሰጥ የኢትዮጵያ ስኳር ኢንዱስትሪ ድጋፍ ሰጪ ማዕከል አክስዮን ማህበር በሶስቱ ስኳር ፋብሪካዎች፣ በልማት ባንክ እና በመድኅን ድርጅት በአክስዮን መልክ ህዳር 1990 ዓ.ም ተቋቋመ፡፡
6. በመቀጠልም አራተኛውና በአፋር ብሔራዊ ክልል የሚገኘው የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ በደንብ ቁጥር 122/98 እንዲቋቋም ተደረገ፡፡ፋብሪካው በ 50 ሺህ ሄክታር ላይ የሚለማ የሸንኮራ አገዳ መሬት

እንዲኖረው እና ዓመታዊ የስኳር ምርት መጠኑ 619,000 ቶን እንዲሁም ዓመታዊ የኤታኖል ምርቱ 63 ሚሊዮን ሊትር እንዲሆን ታቅዶ የተጀመረ ፕሮጀክት ነው፡፡

7. በኋላም የድጋፍ ሰጪ ማዕከሉን በማፍረስ የኢትዮጵያ ስኳር ልማት ኤጀንሲ በአዋጅ ቁጥር 504/98 ተቋቁሞ የስኳር ፋብሪካዎቹን በመቆጣጠር፣ በፕሮጀክት ልማት፣በምርምር፣በስልጠናና በግብይት ረገድ ድጋፍ ሲሰጥ ቆየ፡፡ ይሁንና ከጥቅምት 19 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ ኤጀንሲው እንዲፈርስ ተደርጎ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 192/2003 የአሁኑ ስኳር ኮርፖሬሽን ተቋቋመ፡፡ ኮርፖሬሽኑ የስኳር ልማትን በአገራችን በስፋት ለማካሄድ በሚያስችለው መልኩ ተደራጅቶ ተግባራዊ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

8. አራተኛው በአፋር ብሔራዊ ክልል የሚገኘው የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ በደንብ ቁጥር 122/98 እንዲቋቋም ተደረገ፡፡ፋብሪካው በ 50 ሺህ ሄክታር ላይ የሚለማ የሸንኮራ አገዳ መሬት እንዲኖረው እና ዓመታዊ የስኳር ምርት መጠኑ 619,000 ቶን እንዲሁም ዓመታዊ የኤታኖል ምርቱ 63 ሚሊዮን ሊትር እንዲሆን ታቅዶ የተጀመረ ፕሮጀክት ነው፡፡

9. በአዋሽ ተፋሰስ ዝቅተኛው አከባቢ በአፋር ብሔራዊ ክልል በ50ሺህ ሄክታር መሬት ላይ የሚለማ የሸንኮራ አገዳን በግብዓትነት የሚጠቀመው የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ከአዲስ አበባ በ670 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል፡፡

10. በግዙፍነቱ እና በተሻለ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚነቱ ጭምር ከሌሎቹ ነባር ስኳር ፋብሪካዎች የሚለየው ይህ ፋብሪካ ከአገሪቱ መዲና በስተምስራቅ ወደ ጅቡቲ የሚወስደውን መንገድ ተከትሎ ከጂቡቲ ወደብ በ300 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ይህ ምቹ ሁኔታም ወደፊት የፋብሪካውን ምርት ወደ ውጭ ለመላክ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡በ1998 ዓ.ም የፕሮጀክት ሥራው የተጀመረው የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ይዞታ በሚሌ፣በዱብቲ፣በአሳይታ እና በአፋምቦ ወረዳዎች ውስጥ ይገኛል፡፡ የግንባታ ምዕራፍ በሁለት ተከፍሎ የሚካሄደው የዚህ ፋብሪካ የመጀመሪያው ምዕራፍ ግንባታ ተጠናቆ ከጥቅምት 2007 ዓ.ም ጀምሮ ተንዳሆ አንድ ወደ ማምረት የተሸጋገረ ሲሆን፣በሙሉ አቅሙ ማምረት ሲጀምር በቀን 13ሺህ ቶን አገዳ ይፈጫል፡፡የምርት መጠኑም ደረጃ በደረጃ እያደገ በዓመት ከ300ሺህ ቶን ወይም ከ3 ሚሊዮን ኩንታል ስኳር በላይ እንደሚደርስ ይጠበቃል፡፡በተመሳሳይ በሁለተኛ ምዕራፍ የሚገነባው የተንዳሆ ቁጥር ሁለት ፋብሪካ በቀን 13ሺህ ቶን አገዳ እየፈጨ በዓመት ከ3ሚሊዮን ኩንታል ስኳር በላይ የማምረት አቅም ይኖረዋል፡፡ በአጠቃላይ ተንዳሆ አንድና ሁለት በጋራ በቀን 26ሺህ ቶን አገዳ የመፍጨትና በዓመት ከ6ሚሊዮን ኩንታል ስኳር በላይ የማምረት አቅም አላቸው፡፡በተጨማሪም ከስኳር ተረፈ ምርት ማመንጨት ይችላሉ ተብሎ ከሚገመተው 120 ሜጋ ዋት የኤለክትሪክ ኃይል ውስጥ ለአገሪቱ ማዕከላዊ የኤሌክትሪክ ኃይል ማከማቻ 76 ሜጋ ዋቱን በማስገባት ዘርፈ ብዙ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታቸውን ያረጋግጣሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡እንዲሁም በጋራ 63 ሚሊዮን ሊትር ኤታኖል

ለማምረት ያላቸው አቅምም ይጠቀሳል፡፡ለፋብሪካው ከሚያስፈልገው 50ሺ.ህ ሄክታር መሬት ላይ ከሚለማ የሾንኮራ አገዳ ውስጥ 25ሺ.ህ ሄክታሩ የሚለማው በአከባቢው በሚገኙ አገዳ አብቃይና አቅራቢ አርብቶ አደሮች ሲሆን፣ማምረት ለጀመረው ተንዳሆ አንድ ከሚያስፈልገው 25ሺ.ህ ሄክታር መሬት ውስጥ በፋብሪካው አማካኝነት እስከ ህዳር 30/2007 ዓ.ም ድረስ ከ19ሺ.ህ ሄክታር መሬት በላይ ለምቷል፡፡

11. የአገዳ ልማቱ የሚከናወነው በአዋሽ ወንዝ ላይ በተሰራው የተንዳሆ ግድብ አማካኝነት ነው፡፡ ከ1.86 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ውኃ በላይ የመያዝ አቅም ያለው ይህ ግድብ ከ60ሺ.ህ ሄክታር መሬት በላይ ማልማት ይቻላል፡፡ፋብሪካው በመስኖ የሚለማ መሬት ለአከባቢው አርብቶ አደሮች በማመቻቸቱም አርብቶ አደሩ ወደ ክፍል አርሶ አደርነት መሸጋገር የቻለበት ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮ ተጠቃሚ መሆን ጀምሯል፡፡ ፋብሪካው ወደ ሙሉ አቅሙ ማምረት ሲገባ 50ሺ.ህ ለሚሆኑ ዘጎች የሥራ ዕድል ይፈጥራል፡፡

## የስኳር ኮርፖሬሽን ራዕይ እና ተልዕኮ

### ራዕይ

12. በቀጣይ እድገት ላይ በመመስረት በ2016 ዓ.ም በዓለም ተወዳዳሪ ከሆኑ 10 ግንባር ቀደም የስኳር ኢንዱስትሪዎች ተርታ መሰለፍ፣

### ተልዕኮ

13. በአገሪቱ ያለውን እምቅ ሃብት ለማልማት የሚያስችል ዘመናዊ ቴክኖሎጂና የሰው ሀይል አቅም በማፍራት ስኳር፣የስኳር ተረፈ ምርትና ተጓዳኝ ምርቶችን በማምረት የአገር ውስጥ ፍላጎትን ከማርካት ባሻገር የጎላ የኤክስፖርት ድርሻ በመያዝ የአገሪቱን እኮኖሚ መደገፍ፡፡

### የስኳር ኮርፖሬሽኑ ዓላማዎች

14. በሚኒስትሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር 192/2003 የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው

- የሸንኮራ አገዳና ስኳር የሚያስገኙ ሌሎች ሰብሎችን ማልማት፣
- ስኳር፣ የስኳር ውጤቶችን፣ የስኳር ተረፈ ምርቶችን እና የስኳር ተረፈ ምርት ውጤቶችን በፋብሪካ ማዘጋጀትና ማምረት፣
- ምርቶቹንና ተረፈ ምርቶቹን ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ማቅረብ፣
- አዳዲስና የማስፋፊያ የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች የአዋጭነት ጥናት፣ የዲዛይን ዝግጅት፣የቴክኖሎጂ መረጣና ድርድር፣የተከላ ኮሚሽኒንግ ሥራዎች እንድካሄዱ ማድረግ፣
- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በሸንኮራ አገዳና በስኳር አመራረት ቴክኖሎጂ ጥናትና ምርምር ማካሄድና ጠቃሚ ውጤቶችን በሥራ ላይ ማዋል፣

- አቅሙ ካላቸው የሀገር ውስጥ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ለመንግሥት የስኳር ፋብሪካዎች የሚያስፈልጉ የማምረቻ መሣሪያዎችና መለዋወጫዎች ዲዛይንና ፋብሬኬሽን ሥራዎች በሀገር ውስጥ እንዲከናወኑ ማድረግ፤
- በሕግ መሠረት ለሥራው የሚያስፈልገው መሬት ባለይዞታ መሆንና ማልማት፤
- የአገዳ ምርታቸውን ለመንግሥት የስኳር ፋብሪካዎች የሚያቀርቡ አገዳ አብቃዮችን ማበረታታትና መደገፍ፤
- ለስኳር ኢንዱስትሪ የሚፈለገውን የሰለጠነ የሰው ኃይል በሚፈለገው ዓይነት፣ መጠንና ጥራት ለማፍራት እንዲቻል ከሚመለከታቸው የትህምርት ተቋማት ጋር መተባበር፤
- ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጂ ሥራዎችን መሥራት ናቸው፡፡

## የኮርፖሬሽኑ መብትና ግደታዎች

15. በሚኒስትሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር 88/1992 ተቋቁሞ የነበረው የመተሐራ ስኳር ፋብሪካ፤ በሚኒስትሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር 89/1992 ተቋቁሞ የነበረው የወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ፤ በሚኒስትሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር 199/1994 ተቋቁሞ የነበረው የፊንጫአ ስኳር ፋብሪካ፣ የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 122/98 እና በአዋጅ ቁጥር 504/2006 ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ ስኳር ልማት ኤጀንሲ መብትና ግደታዎች በደንብ ቁጥር 192/2006 ለኮርፖሬሽኑ ተላልፈዋል፡

## የነባር ስኳር ፋብሪካዎች የማስፋፊያ ሥራዎች ተቋራጮች ኃላፊነት

16. ከተቋራጭ የሚጠበቁ ኃላፊነቶች እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

1. በገባው ውል መሰረት ዲዛይን መሥራት ፣መፈብረክ በተጨማሪም ለግዥ የሚሆኑ ማቴሪያሎችን ማዘጋጀት፣ንዑስ ኮንትራት/ሰብ ኮንትራክት/ መስጠት፣ፋብሪካ ተከላ ማካሄድ እና ለፋብሪካው እንቅስቃሴ የሚያስፈልጉ ምቹ አቅርቦቶችን በጥንቃቄና በትጋት በውሉ መሰረት አሟልቶ መገኘት፣
2. ተቋራጩ የኮንትራት ውል ሰጪው ድርጅት ያቀረበለትን ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ዳታዎችን /በመስክም በመገኘት ጭምር/በጨረታው አሸናፊነቱ በተሰጠው ከ28 ቀናት ውስጥ በሚገባ መርምሮ ኮንትራት ውል ማፅደቅ አለበት፣
3. ተቋራጩ ለሥራው የሚያስፈልጉትን መሳሪያዎች አሟልቶ ውል ከገባበት ቀን ጀምሮ ወደ ሥራ በመስማራት ማጠናቀቅ በሚገባው ጊዜና የኮንትራት ዋጋ ማጠናቀቅ ናቸው፡፡

## በነባር ስኳር ፋብሪካዎች የማስፋፍያ ሥራዎች

### ከአማካሪ መሀንዲሶች የሚጠበቁ ተግባራት

17. ከአማካሪ መሀንዲስ የሚጠበቁ ሶስት ኃላፊነቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል

1. አማካሪ ድርጅቱ ከተቋራጭ ጋር በሚያደርገው የየቀን ግንኙነት ሥራዎችን በእቅድ በመምራት ትክክለኛው ዲዛይን ሥራ ላይ መዋሉን ክትትል ማድረግ፣
2. ተቋራጭ የፋብሪካ ግንባታና ተከላን በሚገባ ማከናወኑን ግምገማ በማድረግ ማረጋገጥ፣
3. ሥራው በታቀደለት ጊዜ እንዲጠናቀቅ በእቅድ መሰረት እየተከናወነ ስለመሆኑ በየሳምንቱ

በመደበኛ ፕሮግራም የፕሮጀክት ግምገማ ማከናወን ናቸው፡፡

## የስኳር ኮርፖሬሽን ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ሃይል

18. **የስኳር ኮርፖሬሽኑ አደረጃጀት**

ኮርፖሬሽኑ በአንድ ዋና ዳይሬክተር የሚመራ ሲሆን በስሩ የሚከተሉትን የሥራ ዘርፎች ይዞ ይገኛል፡፡ እነርሱም፡- የኮርፖሬት ምክርና ድጋፍ አገልግሎት ዘርፍ፣ኮርፖሬት ኦዲት፣ኮርፖሬት ትራንስፎርሜሽንና ካይዘን ዘርፍ፣ኮርፖሬት መረጃና አይቲ ዘርፍ፣የአገዳ ተክል ልማትና ፋብሪካ ግንባታ ዘርፍ፣ ኦፕሬሽን ዘርፍ፣ኮርፖሬት እቅድና ፕሮጀክት ዘርፍ፣ኮርፖሬት ግዥና ንብረት አስተዳደር ዘርፍ፣ ኮርፖሬት የህዝብ ተሳትፎ ዘርፍ፣ ኮርፖሬት ፋይናንስ ዘርፍ፣ኮርፖሬት ሰው ሀብት አመራርና ልማት ዘርፍ፣ኮርፖሬት ግብይት ዘርፍ፣ምርምርና ስልጠና ዘርፍ እና መስኖ፣ቤቶችና መሰረተ ልማት ዘርፍ ሆነው በስራቸው በአወቃቀር መግለጫው መረዳት እንደሚቻለው በዳይሬክቶሬቶች የተዋቀረ ነው፡፡

**ስኳር ኮርፖሬሽን የሰው ሃይል/2008 ዓ.ም/**

| ተ.ቁ | የፋብተሪካው /የፕሮጀክቱ ስም | በመዋቅርየተፈ ቀደየሰው ኃይል | በስራ ላይ ያለ የሰው ኃይል | ያልተሸፈኔ የስራ መደብ ብዛት | ከመዋቅር በላይ ያለ የሰው ኃይል | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ተንዳሆ | 9,757 | 3,493 | 6,264 | | |
| 2 | ወንጂ/ሸዋ | 2,605 | 3,726 | | 1,121 | |
| 3 | መተሐራ | 2,514 | 3,203 | | 689 | |
| 4 | ፊንጫአ | 3,205 | 3,270 | | 65 | |
| | አጠቃላይ | 18081 | 13692 | 6264 | 1875 | |

ማስታወሻ፡- በሥራ ላይ ያለው የሰው ሃይል ቋሚ እና ኮንትራትን ጨምሮ ነው፡፡

## የስኳር ኮርፖሬሽን የፋይናንስ ምንጭ

19. ለኮርፖሬሽኑ የተፈቀደው ካፒታል ብር 41,999,731,264(አርባ አንድ ቢሊዮን ዘጠኝ መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሚሊዮን ሳባት መቶ ሰላሳ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ስድሳ አራት ብር) ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ብር 6,042,512,614( ስድስት ቢሊዮን አርባ ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ አስራ ሁለት ሺህ ስድስት መቶ አስራ አራት ብር) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፊለዋል፡፡

ከ2006 እስከ 2008 በጀት ዓመታት ያለው የኮርፖሬሽኑ የበጀት አጠቃቀም የፋይናንስ ምንጭ

በአባሪ ቁጥር ሁለት ተያይዟል፡፡

**የኮርፖሬሽኑ የአሰራር ስርዓት መግለጫ/System Description/** :- በአባሪ ቁጥር ሶስት ተያይዟል፡፡

## የኦዲቱ ዓላማ :-

20. የስኳርኮርፖሬሽን በነባር ስኳር ፋብሪካዎች ላይ ያካሄዳቸውን የማስፋፍያ ሥራዎች አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፣ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆናቸውን መገምገም ሲሆን በተለይ ኦዲቱ በማስፋፍያ ዕቅድ የተያዙ የነባር ማስፋፍያ ሥራዎች፣የፋብሪካ ማስፋፍያ ግንባታ፣ተከላና የኮሚሽኒንግ ሥራዎች፣የመስኖ ግድብና አውታር ግንባታ ማስፋፍያ ሥራዎችን አፈፃፀም እና ከማስፋፍያ በኃላ ያለው የኦፕሬሽን አፈፃፀም ውጤታመነትን በመገምገም በአሠራር ላይ ያጋጠሙ ችግሮች ከነበሩ በመለየት ችግሮቹ የሚቀረፉበትን ወይም የሚሻሻሉበትን የማሻሻያ ሀሣቦች ለማቅረብ እና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

## የኦዲቱ አካባቢ

21. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አከባቢ/Potential Audit area/ የስኳር ኮርፖሬሽን በነባር ስኳር ፋብሪካዎች ባካሄዳቸው የማስፋፍያ ሥራዎች በተለይ በእርሻና የፋብሪካ ማስፋፍያዎች አፈፃፀም፣ከማስፋፍያ በኃላ ያለው የኦፕሬሽን አፈፃፀም፣ለማስፋፍያ አፈፃፀም የሚያስፈልጉ ግብዓቶች አቅርቦት እንዲሁም ከማስፋፍያ ሥራዎች ጋር የተያያዙ የምርምርና ሥልጠና እና የአከባቢ ጥበቃ ሥራዎች አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፣ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ ስለመከናወናቸው እና የማስፋፍያ ሥራዎችም ግልጽነት እና ተጠያቅነትን ባጠናከረ መልኩ የተካሄዱ ስለመሆናቸው ለመገምገም ነው፡፡

## የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች እና መመዘኛ መስፈርቶች፡-

22. ከላይ በተመረጠው የኦዲት አካባቢ /Potential Audit area/ሥር አራት የትኩረት አቅጣጫ /Audit Issues/ እና አምስት ንዑስ የትኩረት አቅጫዎች /Audit Sub Issues/ ተለይተዋል፡፡ እነርሱም፡-

1. የነባር ስኳር ፋብሪካዎች የእርሻና የፋብሪካ ማስፋፊያዎች አፈፃፀምን መገምገም
   1.1 የፋብሪካ ግንባታና ተከላ አፈፃፀምን መገምገም
   1.2 የእርሻ ማስፋፊያ ሥራዎች አፈፃፀምን መገምገም
   1.3 ኮርፖሬሽኑ በሸንኮራ አገዳ ልማት የእርሻ መስፋፋት ምክንያት ለተነሱ/ ለሚነሱ የመሬት ባለይዞታዎች ካሳ ለሚገባቸው የካሳ ክፍያ የፈፀመ መሆኑን መገምገም
2. የነባር ስኳር ፋብሪካዎች ከማስፋፊያ በኋላ ያለውን የኦፕሬሽን ሥራዎች አፈፃፀምን መገምገም
   2.1 የሸንኮራ አገዳ ልማት የእርሻ ኦፕሬሽን አፈፃፀምን መገምገም
   2.2 የፋብሪካ ኦፕሬሽን አፈፃፀምን መገምገም
3. ለፋብሪካ ማስፋፊያ ግንባታና ተከላ፣ ለመስኖ ግድብና ቦዮች እና የቤቶች ግንባታዎች የተገዙ ዕቃዎች/Materials/ የግዥ አፈፃፀም፣ አያያዝ፣ አጠቃቀምና አወጋገድ የስኳር ኮርፖሬሽኑ ባዘጋጀው የግዥ አፈፃፀም እና የንብረት አስተዳደር መመሪያዎች መሰረት የተፈፀመ መሆኑን መገምገም
4. በስኳር /ኢታኖል ፋብሪካዎች የሚገኙ የምርምርና ስልጠና ጣቢያዎች በምርምር ውጤታቸው የስኳር/ኢታኖል ምርትን ከመጨመር አንፃር ያስገኙትንፋይዳ እና ከፋብሪካዎች ማስፋፋት ሥራ ጋር የአካባቢ ጥበቃ እንክብካቤ እየተሰራ መሆኑን መገምገም የሚሉት ናቸው፡፡

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርት እና የተዘጋጀባቸው ማስረጃዎች፡-

23. እነዚህንም የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች እና ንዑስ የኦዲት የትኩተረት አቅጣጫዎች ለመመዘን የሚረዱ 42 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች/Evaluative Criteria/ የተዘጋጁ ሲሆን፤በተዘጋጁትም የመመዘኛ መስፈርቶች ላይ የስኳር ኮርፖሬሽን ኃላፊዎች አስተያት እንዲሰጡበት ተሰጥቷቸው አስተያየታቸውን ያልሰጡ መሆኑ ታውቋል፡፡ መመዘኛ መስፈርቶቹም ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 1 ተያይዘዋል፡፡

- የስኳር ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 192/2003
- የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች
- የስኳር ኮርፖሬሽን የአዲስ ሥራ ሂደት ቀረፃ/ቢፒ አር ሰነድ/ የካቲት 2004 ዓ.ም
- የስኳር ኮርፖሬሽን የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ሀምሌ 2003 ዓ.ም
- የስኳር ኮርፖሬሽን የንብረት አስተዳደር መመሪያ ጥቅምት 2005 ዓ.ም
- ለህዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትን እና ለንብረት ካሳ የሚከፈልበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 455/1997

- የንብረት ካሳ ክፍያ አፈፃፀምን በተመለከተ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የወጣ ደንብ 135/99
- የውስጥ ኦዲት ሪፖርቶች ከ2006- 2008 ዓ.ም የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ እና የስኳር ኮርፖሬሽን/
- የሥራ አፈፃፀም ሪፖርቶች / ከ 2006- 2008 ዓ.ም የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ/
- አካባቢ ጥበቃን ከሚመለከት አዋጅ
- መልካም ተሞክሮዎችን በማካተት የተዘጋጀ ነው፡፡

**የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ፡-**

## የኦዲቱ ወሰን (Audit Scope)

24. ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች እና ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2008 (እንደተሻሻለው) በተሰጠው ሲልጣን መሠረት ነው፡፡ የክዋኔ ኦዲቱ የሚሸፍነው ከ 2006 እስከ 2008 በጀት ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ በስኳር ኮርፖሬሽን የነባር ስኳር ፋብሪካዎች የማስፋፊያ ሥራዎች አፈፃፀምና ውጤታማነትን  በተመለከተ የተሰራውን ሥራ ነው፡፡ የክዋኔ ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በስኳር ኮርፖሬሽን ሲሆን፣ በስሩ  ባለ  በተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ነው፡፡

## የኦዲቱ ዘዴ

25. በስኳር ኮርፖሬሽና የስኳር ፋብሪካው ግንባታ እና ተከላው በተከናወነበት ተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ በመገኘት አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች በመከለስ፣ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ጋር በመገናኘት ቃለ-መጠይቅ በማድረግ  እና በአካል በመገኘት መረጃዎችንና ማስረጃዎችን በመሰብሰብ እና በመተንተን የክዋኔ ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡

## ክፍል ሁለት
## ግኝቶች
## ለስኳር ፋብሪካ ግንባታና ተከላ የጨረታ ሂደትና ድርድር መደረጉን በተመለከተ

26. ኮርፖሬሽኑ ለነባር ስኳር ፋብሪካዎች ማስፋፊያ ግንባታ የጨረታ ሂደትና ድርድር ሊያከናውን ይገባል፡፡

27. ኮርፖሬሽኑ ለተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ግንባታና ተከላ የጨረታ ሂደትና ድርድር ያከናወነ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፣የጨረታ ሂደቱን የሚያመለክቱ ማስረጃዎች የቀረቡ ቢሆንም፣ለአማካሪው ጄፒ ሙከህርጂ/J.P MUKHERJI/ የተቋራጩ የሥራ ሂደት ክንውንን በተመለከተ በቀረበለት ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ በሥራ ሂደት ያጋጠመው ችግር የጨረታ ሰነዱ እያንዳንዱን የሥራ ፓኬጅ በተናጠል መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ በመሆኑ ኢፒሲ/EPC/ ለተባለው ድርጅት የተጠቃለለ ሥራ የኮንትራት ውል አለመሰጠቱ መሆኑን ገልፆ በተናጠል በየፓኬጁ የተደረገው ጨረታ ሂደት ከተገመገመ በኋላ EPC የተባለው ተቋራጭ እንደዋና አሰሪ ሆኖ ሌሎቹ የጨረታ አሸናፊዎች በእሱ ስር /Sub- Contractors/ ሆነው የጨረታው ዋጋ ጭማሪ በማያሳይበት/Fixed Price/ በሆነ መልኩ እንዲሰሩ በቀጣሪው ድርጅት የተወሰነ ሲሆን፣ ሆኖም በዋናነት እንዲመራ የተደረገው EPC ተቋራጭ እያንዳንዱ የጨረታ ተወዳዳሪ የአስተዳደር ክፍያ እንዲከፍለው በመጠየቁ ጭቅጭቅ ተነስቶ በሁለት የጨረታ ተወዳዳሪዎች ክስ በመመስረቱ ጉዳዩ ወደ ህግ የቀረረበት ሁኔታ የደረሰ ሆኖ የ EPC የኮንትራት ውል እ.ኤ.አ ጥር 2008 የተፈረመ ቢሆንም ሥራ ላይ ሊውል የቻለው ከ 18 ወራት በኋላ እ.ኤ.አ ሀምሌ 17/2009 መሆኑን ገልፀዋል፡፡

28. ስለሁኔታው ለፋብሪካው ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበ ቃለ-መጠይቅ መልስ የሰጠ አካል ያልተገኘ መሆኑ ታውቋል፡፡

29. በስኳር ኮርፖሬሽን የፋብሪካ ግንባታና ኦፕሬሽን ከተሰጠው ተግባር በሀገር በቀል አቅም በወቅቱ አስተማማኝና አዋጭ የሆነ የፕሮጀክት ድርድር ማከናወን መቻል ከሚለው አኳያ ባለመተግበሩ የስኳር ፋብሪካ ግንባታና ተከላውን በተናጠል ፓኬጅ አወዳድሮ በጨረታ ሂደቱ ቀድሞውኑ ያልተገለጠን ሀሳብ በራስ ፍላጎት ከመሀል አንድ መርጦ በመሾም ሌሎቻችሁ በሱ ስር ሆናችሁ ስሩ በሚል ሂደት ለማሰራት በመሞከሩ ወደ ክስ ሂደት በማድረስ በፋብሪካው የሥራ ሂደት ላይ የጊዜ መጓተት ብክነት እንዲኖር አድርጓል፡፡

## ለሸንኮራ አገዳ ተክል ልማት የመሬት ርክክብ መፈፀሙን እና የማሽነሪ አቅርቦት በማሟላት የመሬት ዝግጅት መደረጉን በተመለከተ

30. ኮርፖሬሽኑ ለነባር ስኳር ፋብሪካዎች ለሸንኮራ አገዳ ተክል ልማት የመሬት ርክክብ ሊፈፅም፣ የማሽነሪ አቅርቦት እንዲሟሉ ሊያደርግ፣ ለአገዳ ልማቱ የመሬት ዝግጅት የማለስለስ/Fine Level/ ሥራን ሊደግፍ፣ ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

31. ኮርፖሬሽኑ ለነባር ስኳር ፋብሪካዎች ማስፋፊያ ለሸንኮራ አገዳ ተክል ልማት የመሬት ርክክብ በመፈፀም እና የማሽነሪ አቅርቦት እንዲሟሉ በማድረግ ለአገዳ ልማቱ የመሬት ዝግጅት/Fine level/ ለተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ያደረገ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፡- በተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ የእርሻ ኦፕሬሽን በ2006 በጀት ዓመት 16,882 ሄክታር የግርድፍ መሬት ርክክብ ለመፈፀም ታቅዶ 6,953.70/41.19%/ ሄክታር ርክክብ የተፈፀመ ሆኖ 16,882 ሄክታር ውሃ ገብ መሬት ርክክብ ለመፈፀም ታቅዶ 6,434.21/38.11%/ ሄክታር ርክክብ የተፈፀመ መሆኑ ታውቋል፡፡

32. ይሁን እንጂ ከውሃ ሥራዎች ርክክብ የሚደረጉ ማሳዎች ቀጣይ ሥራዎችን/ኦፕሬሽኖች/ ለመሥራት የሚፈለገውን ጥራት መሰረት ያላደረጉ በመሆኑ እና ርክክብ ሲደረግ ይህ ችግር እያለባቸው እንዲስተካከሉ በአስተያየት በመፈራረም ቢሆንም ተመልሰው የማስተካከያውን ሥራ ከመሥራት ይልቅ ሌላ አዲስ ሥራ የሚጀምሩ በመሆኑ ሥራው ሳይጠናቀቅ ባለበት ሁኔታ ወደ ቀጣይ ሥራ/ኦፕሬሽን/ ለመግባት አዳጋች የነበረ መሆኑ ታውቋል፡፡

33. የእርሻ ኦፕሬሽን አፈፃፀምን በተመለከተ በ 2006 በጀት ዓመት 16,882 ሄክታር መሬት ድልዳሎ ለማከናወን በእቅድ ተይዞ አፈፃፀሙ 8,251.30/48.87%/ ሄክታር መሆኑ ታውቋል፡፡

34. ከ 2006 በጀት ዓመት እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት መረዳት እንደተቻለው ለአፈፃፀም ልዩነት መንስዔ የሆኑት እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

    1. የግሬደር ማሽኖች የቀን ውጤታማነታቸው አነስተኛ መሆን/የግሬደር ማሽን በአማካይ በቀን 16.8 ( ለ 81 የሥራ ቀናት ) ወደ ሥራ እንዲመጡ ቢደረግም 1,025.9 ሄክታር ብቻ( በቀን በአማካይ 12.65 ሄክታር ) የመሬት ድልዳሎ በመሥራት ከወጣው የማሽን ብዛት አንፃር ዝቅተኛ አፈፃፀም የነበረ መሆኑ፣
    2. የቨርሳታይል ማሽኖች የቀን ውጤታቸው አነስተኛ መሆን በአማካይ 4.52 ( ለ 95 የሥራ ቀናት) ወደ ሥራ እንዲወጡ የተደረገ ሲሆን 618 ሄክታር በማከናወን አነስተኛ የሥራ አፈፃፀም ያሳዩ መሆኑ፣

3. የቨርሳታይል ማሽኖች የአውቶ ሲስተም ሬንጃቸው አነስተኛ መሆን እና ሃይድሮሊክ ሲስተም/የፈሳሽ ግፊት አሰራር ዘዴ/ በተደጋጋሚ ችግር ማጋጠሙ፣
4. የኤስ.ቲ.ኤክስ ማሽኖች በእርጅና ምክንያት ለተደጋጋሚ ብልሽት የተጋለጡ መሆኑ ታውቋል፡፡

35. በ2006 በጀት ዓመት16,882 ሄክታር መሬት የኮሜርሻል/የፋብሪካ ግብዓት/ አገዳ ተከላለማከናወን ታቅዶ 8,220/48.69%/ ሄክታር የተተከለ መሆኑ ታውቋል፡፡ የእቅዱ አለመሳካት ምክንያቶች፡-

- የግርድፍ እና የውሃ ገብ መሬት ርክክብ በውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት የሚከናወን እና ሥራው ሲጠናቀቅ ለድርጅቱ የሚተላለፉ በመሆኑ ቀጣይ ኦፕሬሽኖች በዚህ ሥራ ላይ የወደቁ በመሆኑ፣
- ውሃ ገብ ተብለው ወደ ፋብሪካው የሚተላለፉ መሬቶች የመስኖ አውታሮቹ የአፍ ቴክ/መቀነሻ/ ችግር ያለባቸው ውሃ መሸከም የማይችሉ ሁለተኛ/ሰከንደሪ/ና ሶስተኛ/ቴሪሸሪ/ የውሃ ማሳለፊያ ቦዮች/ካናሎች/ በመገንባታቸው በቀላሉ ውሃ በሚገባ ጊዜ ካናሎቹ በውሃ የሚሸረሸሩና የሚሰበሩ መሆኑ ታውቋል፡፡

36. ከ2007 በጀት ዓመት እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በተገኘው መሰረት፡-በ 2007 በጀትዓመት 10,521 ሄክታርየ ግርድፍ መሬት ርክክብ ታቅዶ ከንውኑ 2,980/28.32%/ ሄክታር ሲሆን የክንውኑ ማነስ ምክንያቶች፡-

1. የግርድፍ መሬት በውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ርክክብ ተፈፅሞ ወደ ድርጅቱ የሚተላለፍ በመሆኑ/የመዘግየት ሁኔታ/ መኖሩ፣
2. የግርድፍ መሬት አቅርቦትን በተመለከተ ፋብሪካው 22 ዶዘሮቸ ያሉት ሲሆን፣ 16ቱ የመለዋወጫ ችግር የገጠማቸው በመሆኑ 6ቱ ብቻ በሥራ ላይ በመዋላቸው እና ዶዘሮቹ የሰርቪስ ኪት የሚፈልጉ በመሆናቸው በግርድፍ ሥራ አቅርቦት ላይ ለዝቅተኛ አፈፃፀም አስተዋፆ ማድረጋቸው የታወቀ ሲሆን፣ እንዲሁም የውሃ ገብ መሬት 10,521 ሄክታር ለመረከብ ታቅዶ ክንውኑ 2,654/25.23%/ሄክታር መሆኑ ታውቋል፡፡ ለአፈፃፀሙ ማነስ ምክንያቶች ከግርድፍ መሬት ርክክብ ጋር የሚመሳሰል መሆኑ ተገልጿል፡፡
3. በተጨማሪም ለተንዳሆ የአገዳ እርሻ ልማት በመሰረታዊነት እንዲያገለግል ታስቦ የተሰራው የተንዳሆ ግድብና መስኖ ሥራ ፕሮጀክት በቀድሞው የኢትዮጵያ ውሃ ሥራዎች ድርጅት በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን የውሃ መሰረተ ልማት ኮንስትራክሽን ዘርፍ የፕሮጀክቱ ግንባታ በመስከረም ወር 1997 ዓ.ም በብር 840,254,270.70/ስምንት መቶ አርባ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሃምሳ አራት ሺህ ሁለት መቶ ሰባ ከ 70/100 / የውል ስምምነት ተፈፅሞ በ 24 ወራት/በ 1999 ዓ.ም/ ጊዜ ውስጥ እንደሚጠናቀቅ ታስቦ ግንባታው የተጀመረ ሲሆን፣ በነሀሴ 2007 ዓ.ም/8 ዓመት ዘግይቶ/

የተጠናቀቀ ሲሆን፤ በ 2003 ዓ.ም የውለታ ማሻሻያ ተደርጎ የኮንትራት ዋጋውም ወደ 4.15 ቢሊዮን ከፍ እንዲል የተደረገ መሆኑ ለውሃ ሥራዎች ኮርፖሬሽን የውሃ መሰረተ ልማት ኮንስትራክሽን ዘርፍ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበ ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ ተገልጿል፡፡ ይህም በተንዳሆ የሸንኮራ አገዳ ልማት መሬት ርክክብ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያሳደረ መሆኑ በፋብሪካው የእርሻ ክፍል ሰራተኞች በተደጋጋሚ ተገልጿል፡፡



በተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ለሸንኮራ አገዳ እርሻ ልማት ሊውሉ የመጡ አዲስ ማሽነሪዎች ለ30 ሰዓት ሰርተው በብልሽት ምክንያት የቆሙ የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ፡፡

37. በ2007 በጀት ዓመት 10,521 ሄክታር የኮሜርሻል አገዳ ተከላ ለማከናወን ታቅዶ የተከላው ክንውን 1316/12.51%/ ሄክታር መሆኑ ታውቋል፡፡
የአፈፃፀሙ ማነስ ምክንያቶች የመሬት ዝግጅት ሥራውን የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን በሚጠበቀው ደረጃ ባለመሥራቱ ምክንያት ቀጣይ የኦፕሬሽን ሥራ የሆነው አገዳ ተከላም ከመሬት ዝግጅት አፈፃፀም የተለየ ውጤት የማይጠበቅለት በመሆኑ መሆኑ ተገልጿል፡፡

38. ስለ ሁኔታው የተንዳሆ የእርሻ ዘርፍ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ በ2006 በጀት ዓመት በመሬት ርክክብ ረገድ ኮርፖሬሽኑ ከፍተኛ ጥረት ያደርግ የነበረ ሲሆን ከውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ጋር አማካሪው ባለበት የጋራ የውውይትና የግምገማ መድረክ በስትሪንግ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ ችግሮችን በማሳየት የውሃ ሥራዎች ድርጅት ፈጥኖ ሥራዎችን አጠናቆ ውሃ ገብ መሬት እንዲያስረክብ ግፊት ተደርጎ የነበረ መሆኑን ገልፀው ውሃ ሥራዎች ገፍቶ ባልሄደባቸው እና ማስተካከያ መደረግ በሚገባቸው ውሃ ገብ ያልሆኑ መሬቶች በራስ አቅም ለመሥራት ጥረት መደረጉን ገልፀዋል፡፡

39. የእርሻ ኦፐሬሽን ሥራዎች አፈፃፀምን በተመለከተ በወቅቱ እቅድ ሲታቀድ ለመሬት ድልዳሎ ሥራ የሚውል በፋብሪካው እጅ ላይ የነበሩት የኤስ.ቲ.ኤክስ /STX/ማሽኖች ብቻ ሲሆኑ ሌሎች የተጠቀሱት ማሽኖች በጊዜ ሂደት የተጨመሩ እንጂ በዝግጅት ምዕራፉ ተሟልተው የተገኙ እንዳልነበሩ ገልፀዋል፡፡

40. በ2006 በጀት ዓመት የሸንኮራ አገዳ ተከላን በተመለከተ አፈፃፀሙ ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት፡- የግርድፍ እና የውሃ ገብ መሬት በውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት የሚከናወን በመሆኑ መዘግየት በመኖሩ፣

- የማህበረሰብ ችግሮች ፡- የአገዳ ተከላ የማስቆም ሁኔታዎች የነበሩ መሆኑ፣
- ለእቅድ ዓመቱ የታሰበው የመሬት ግኝት በእቅድ ዓመቱ 16,882 ሄክታር ኮሜርሻል አገዳ እንዲለማ ግብ የሚሰጥ ቢሆንም እቅዱ የተቀመጠው ከፒሲ 6 ካምፕ ተጨማሪ የማሳ ሄክታር ውጪ እቅዱን ሊያሳካ የሚችል ተጨማሪ የመሬት ግኝት እንኳን በውሉ ባልታወቀበት ሁኔታ እንደነበር ገልፀዋል፡፡

41. እንዲሁም በ 2007 በጀት ዓመት ኮርፖሬሽኑ የመሬት ርክክብ በውሃ ሥራዎች በኩል እንዲደረግ ግፊት ያደርግ የነበረ ቢሆንም ከ 2,654 ሄክታር በላይ ውሃ ገብ መሬት ሊቀርብ ያልቻለ መሆኑን ገልፀው በበጀት ዓመቱ እንዲፈፀም ከታቀደው 10,521 ሄክታር የመሬት ዝግጅትና የአገዳ ልማት ግብ አንፃር ርክክብ የተረደገው የማሳ ስፋት ከ 25% በላይ ቀጣይ ኦፐሬሽኖች መፈፀም የማያስችል የነበረ መሆኑን አብራርተው ለዚህም ምክንያቱ በወቅቱ ፋብሪካው የነበረው የማሽነሪ ብዛት ከበቂ በላይ ሲሆን ማሽነሪዎች የሚያስፈልጋቸውን መለዋወጫ ከማሟላት አኳያ በኮርፖሬሽን ደረጃ የፋይናንስ እጥረት በመከሰቱ መሆኑን ገልፀው በተጨማሪም በወቅቱ የሚሰሩ እና የተሻሉ ማሽነሪዎችን ለታቀደው ሥራ የማሰመራቱ ሁኔታ የማይጋብዝ በመሆኑ በዋናነት ለጎርፍ መከላከል ሥራ ለአጭር ጊዜ ተብሎ ከእርሻ ዘርፍ ላይ በመውሰድ የተቻለ ቢሆንም የጎርፍ መከላከል ሥራው ወራቶችን የወሰደ በመሆኑ ማሽነሪዎቹ ለታለመለት ዓመታዊ ግብ መሳካት የሚጠበቅባቸውን ሳያበረክቱ መቅረታቸውን ገልፀዋል፡፡

42. በተጨማሪም በ 2007 በጀት ዓመት ከታቀደው 10,521 ሄክታር አኳያ የተፈፀመው የኮሜርሻል አገዳ ተከላ 12.25% ሆኖ የወረደበት ምክንያት የመሬት ዝግጅት ሥራዎች በሚጠበቀው ደረጃ ባለመሰራታቸው ቀጣይ የሆነው አገዳ ተከላም ከመሬት ዝግጅት አፈፃፀም የተለየ ውጤት እንዲኖረው የማይጠበቅ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

43. በስኳር ኮርፖሬሽን የኮርፖሬት እቅድና ግምገማ ዘርፍ ከተሰጠው ተግባር ኮርፖሬሽኑ በወቅቱና በጥራት የተዘጋጀ መሪ እቅድ፣ እስትራቴጂክ እቅድ፣ የኦፕሬሽን እቅድና በጀት እንዲኖር፣ የእቅድ አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ በወቅቱ እንዲከናወን እና በማኔጅመንት የሚሰጡ ግብረ መልሶችና ውሳኔዎች ትግበራ እንዲሆኑ እና የፕሮጀክት ሥራዎች ተቀናጅተው እንዲሰሩና የተቀመጡት ግቦች እንዲሳኩ ከሚለው አኳያ ተግባራዊ ያልተደረገ በመሆኑ በተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ የታቀዱ እቅዶች በኮርፖሬሽኑ እና በስኳር ፋብሪካው በቅንጅታዊ አሰራር ሀብት/ሪሶርስ/ አጠቃቀም ምክንያት በተፈጠሩ ችግሮች ዓመታዊ የግርድፍ መሬት፣ውሃ ገብ መሬት ርክክብና የአገዳ ተከላ እቅዶች እንዳይሳኩ ሆኗል፡፡

## የስኳር ፋብሪካ ግንባታ እና ተከላ ዲዛይን ቁጥጥርና ክትትል እና ግምገማን በተመለከተ

44. ኮርፖሬሽኑ ለነባር ስኳር ፋብሪካዎች ማስፋፊያ የፋብሪካ ግንባታ ዝርዝር ዲዛይን፣ ማሽነሪ አቅርቦት፣የሲቪል ግንባታ ማሽነሪ ተከላና ኮሚሽኒንግ ሥራን ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

45. ኮርፖሬሽኑ ለተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ግንባታ ዝርዝር ዲዛይን፣የማሽነሪ አቅርቦት፣የሲቪል ግንባታ ማሽነሪ ተከላና ኮሚሽኒንግ ሥራን ክትትልና ቁጥጥር ስለማድረጉ፣ እንዲሁም የመስኖ ልማት፣ የሸንኮራ አገዳ ልማትመሬት ድልዳሎ እና ኮሚሽኒንግ ሥራ ፣የቤቶች ልማት ግንባታና አስፈላጊ ማቴሪያል አቅርቦትን የተከታተለና የተቆጣጠረ፣ በታቀደ ጊዜና ወጪ በጥራት መጠናቀቃቸውን ያረጋገጠ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፤ የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ የአንደኛ ምዕራፍ መነሻ የኮንትራት ዋጋ ዩኤስዲ 232,820,699/ሁለት መቶ ሰላሳ ሁለት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሃያ ሺህ ስድስት መቶ ዘጠናዘጠኝ/እና ብር 589,198,859/አምስት መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ሚሊዮን አንድ መቶ ዘጠና ስምንት ሺህ ስምንት መቶ ሃምሳ ዘጠኝ/ ፣ ሁለተኛ ምዕራፍ ዩኤስዲ 139,849,636/አንድ መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሚሊዮን ስምንት መቶ አርባ ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ ሰላሳ ስድስት/ እና ብር 269,205,899/ሁለት መቶ ስድሳ ዘጠኝ ሚሊዮን ሁለት መቶ አምስት ሺህ ስምንት መቶ ዘጠና ዘጠኝ/ ሆኖ የመነሻ ኮንትራት ውል እ.ኤ.አ ጥር 2008 ተፈርሞ በተፈጠረ አለመግባባት ምክንያት ከ 18 ወራት በኋላ እ.ኤ.አ ሐምሌ 17/2009 የተጀመረ ሆኖ የማጠናቀቂያ ጊዜ እስከ እ.ኤ.አ ሚያዚያ/2009 ቢሆንም ባለመጠናቀቁ በሚከተሉት ሁኔታዎች የኮንትራት መነሻ ዋጋ ለውጥ ሳይኖር የማጠናቀቂያ ጊዜ ማራዘሚያ የውል መሻሻያ መደረጉ ታውቋል፡፡የጊዜ ማሻሻያ ውል ያስፈለገባቸው ምክንያቶችና ውል የተደረገባቸው ቀናት እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

5. እ.ኤ.አ 18/01/2010 የማሽን ተከላ ለማከናወን የሲቪል መሰረት ግንባታ ሥራዎች ለማከናወን
6. እ.ኤ.አ 18/03/2014 የስኳር ጁስ መጭመቂያ ክፍልን በሚመለከት
7. እ.ኤ.አ 18/09/2015 መለዋወጫ አቅርቦትን በተመለከተ
8. እ.ኤ.አ 22/06/ 2016 ክለሳ በማድረግ መለዋወጫ አቅርቦትን በተመለከተ /በድምር 6 ዓመት /

እና በዲዛይን ለውጥ ምክንያት በውል ውስጥ የሌሉ በቁጥር 23 ተጨማሪ ሥራዎች ተሰጥተው ተቋራጩ እንዲሰራ የተደረገ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ሆኖም ስለ ምዕራፍ ሁለት ፋብሪካ 31.39% እስከ እ.ኤ.አ 2016 መጠናቀቁን ከሚገልፅ መረጃ በአማካሪው ሙከርጂ ከተሰጠ በስተቀር ማግኘት ያልተቻለ መሆኑ ታውቋል፡፡

46. የሸንኮራ አገዳ የመስኖ ልማት፣ የመሬት ድልዳሎን በተመለከተ በ 2006 በጀት ዓመት የአገዳ ተከላ 16,882 ሄክታር ታቅዶ 8,220/48.69%/ ሄክታር የተተከለ መሆኑ እና የመሬት ድልዳሎ 16,882 ሄክታር ታቅዶ 8,251.30/48.87%/ ሄክታር መከናወኑ የኮሚሽኒንግ ሥራውም ከዚህ አኳያ ሲመዘን አነስተኛ መሆኑ፤እንዲሁም የቤቶች ግንባታን በተመለከተ ለሰራተኛው መኖሪያ የተገነቡ ቤቶች ብዛታቸው 499 መሆኑ ከ 2005/2006 በጀት ዓመት አፈፃፀም ሪፖርት መረዳት የተቻለ ሲሆን፤ ግንባታውን የወሰዱ የተቋራጮች ብዛት 300 ሲሆን በጨረታ ሂደት ተወዳድረው ሥራውን ያከናወኑ ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ ያልተገኘ መሆኑ ታውቋል፡፡

47. ስለ ሁኔታው የፋብሪካ ግንባታና ተከላን በተመለከተ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበ ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ ተቋራጩ በውለታ ውስጥ የሌሉ በዲዛይን ለውጥ ምክንያት 23 ተጨማሪ ሥራዎችን እንዲሰራ በመደረጉ ለጊዜ መጓተት ምክንያት መሆኑን የገለፀ ሲሆን የሸንኮራ አገዳ የመስኖ ልማት የመሬት ድልድልና ኮሚሽኒንግ ሥራ በውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ላይ መሰረት ያደረገ በመሆኑ አፈፃፀሙ ዝቅተኛ መሆኑ በተንዳሆ እርሻ ዘርፍ ኃላፊዎች የተገለፀ ሲሆን፤ የቤቶች ግንባታን በተመለከተ ለተንዳሆ ወኪል የህንፃ ግንባታና ጥገና ቡድን መሪ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበ ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ የቤቶቹን ግንባታ ያከናወኑ 300 በላይ የሆኑ ተቋራጮች መሆናቸው ሲገለፅ፤ የኮንትራት ውላቸው ከሀምሌ 2001 ዓ.ም ጀምሮ ሲሆን ብዙዎቹ በተለያየ ቀን የፈረሙ በመሆኑ የሚያጠናቅቁበት ጊዜ እንደህንፃው ዓይነት ሆኖ በ 10 ወር፣6 ወር፣ በ4ወር፣ በ 3 ወር እና በመሳሰሉት የነበረ መሆኑ ተገልፆ፤ ይሁን እንጂ የግንባታውን ሥራ የወሰዱ ተቋራጮች በጨረታ ስለ መሆኑ ማስረጃ የሌለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡





ከ300 መቶ ባላይ ተቋሯጮች ተሳትፎበት የተሰራ በመፈራረስ ላይ ያለ
የሰራተኞች መኖሪያ ቤትን የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ

48. በስኳር ኮርፖሬሽን የፋብሪካና ኦፕሬሽን ዘርፍ ከተሰጠው ተግባር አስተማማኝና አዋጭ የቴክኖሎጂ መረጣ ማድረግ እና በሀገር በቀል አቅም አስተማማኝና አዋጭ የሆነ የፋብሪካ ግንባታና ኮሚሽኒንግ ሥራ ማከናወን ከሚለው አንፃር ክትትል ባለመደረጉ የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ግንባታና ተከላ እ.ኤ.አ ከ ሐምሌ 17/2009 እስከ እ.ኤ.አ ሰኔ 2016 ድረስ የመጀመሪው ምዕራፍ 94.80% የደረሰ ሆኖ ሁለተኛው ምዕራፍ 31.39%/ ከማጠናቀቂያ ጊዜ ለ 6 ዓመት መዘግየት/፤ የእርሻ ዘርፍ እቅድ አፈፃፀምም አለመሳከትና በቤቶች ግንባታም ለ 499 ቤቶች ከ300 በላይ ተቋራጮች በውል ባልታሰረ ሁኔታ ሥራ ማሰራት በኮርፖሬሽኑ የክትትልና ቁጥጥር ስርዓት እጅግ የላላ መሆኑን ከማሳየቱም በላይ የሀገር ሀብትን ለብልሹ አሰራር ተጋላጭ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

## የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ በታቀደለት ጊዜና በተመደበለት ወጪ መጠናቀቁን በተመለከተ

49. ኮርፖሬሽኑ የክትትልና ቁጥጥር አሰራር ስርዓትን በመዘርጋት እና ተግባራዊ በማድረግ የፋብሪካ ግንባታ በታቀደለት ጊዜና በተመደበለት ወጪ እስከ ኮሚሽኒንግ ሥራ በወቅቱ እንዲጠናቀቅ ሊያደርግ ይገባል፡፡

50. ኮርፖሬሽኑየክትትልና ቁጥጥር ስርዓት ዘርግቶ የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ግንባታ በታቀደለት ጊዜና በተመደበለት ወጪ እስከ ኮሚሽኒንግ ሥራ በወቅቱ እንዲጠናቀቅ ክትትል ያደረገ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ በ 1998 ዓ.ም የፕሮጀክት ሥራው የተጀመረ ሲሆን፤ ፋብሪካው ሁለት ምዕራፍ ግንባታ ያለው ሲሆን፤ የመጀመሪያው ምዕራፍ ግንባታ ጥቅምት 2007 ዓ.ም የምርት ሙከራ ቢያደርግም ሥራው ያልተጠናቀቀ በመሆኑ በ 2008 ዓ.ም ማምረት ያልቻለ መሆኑ ታውቋል፡፡ የሁለተኛው ምዕራፍ ሥራ 31.39% አፈፃም ደረጃ የደረሰ መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

- የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ፕሮጀክትን ለማማከር በጄፒ ሙከርጂ እና በተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ የመነሻ ውል እ.ኤ.አ መስከረም 2006 በመነሻ ዋጋ ዩስዲ 1,328,030 በመፈራረም ሥራው ከ እ.ኤ.አ ህዳር 22/2006 ተጀምሮ እ.ኤ.አ ሚያዚያ 23/2009 እንዲጠናቀቅ የታቀደ ቢሆንም፤ውሉ 3 ጊዜ በመራዘም ፡-
- 1ኛ ማሻሻያ ተጨማሪ የአገልግሎት ሥራ ለመሥራት እ.ኤ.አ ጥር 14/2008 በተደረገ ውል ዩኤስዲ 79,600 ለመክፈል የተወሰነ መሆኑ፣
- 2ኛ ማሻሻያ ፕሮጀክቱ ከአማካሪውና ከቀጣሪው በድርጅት አቅም በላይ የሙከራ ፍተሻ ያልተደረገለት በመሆኑ ለሁለተኛ ጊዜ ሁለቱም ወገኖች ውል ለማሻሻል በዩኤስ ዲ 2,144,885 የተስማሙ መሆኑ፣
- 3ኛ ማሻሻያ ፕሮጀክቱ እስከ እ.ኤ.አ ህዳር 23/2012 ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ባለመጠናቀቁ እስከ እ.ኤ.አ መስከረም 30/2016 የደረሰ በመሆኑ የኮንትራት ዋጋውምዩኤስዲ 7,250,160 ሆኖ ከመነሻ ኮንትራት ዋጋ ዩኤስ ዲ 9,474,645/713.4%/ ጭማሪ ያሳየ ሲሆን በጊዜ በኩልም ሰባት ዓመት የተራዘመ መሆኑ ታውቋል፡፡
- ፕሮጀክቱ ያለበት የአፈፃፀም ደረጃ እ.ኤ.አ ሰኔ/2016 ድረስ ምዕራፍ 1/ፌዝ አንድ/ 94.80% የተጠናቀቀ መሆኑ ሲገለፅ፤ምዕራፍ 2 31.39% መጠናቀቁ ታውቋል፡፡

51. ስለ ሁኔታው በኦዲት ቡድኑ ለተንዳሆ ስኮር ፋብሪካ ኦፕሬሽን ዘርፍ ኃላፊና ለተቋራጭ ለቀረቡ ቃለ-መጠይቆች መልስ መስጠት ያልተቻለ መሆኑ ሲታወቅ፣ ለአማካሪ ድርጅት ለቀረበ ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ በዋናው አሰሪ ተቋራጭ ስር ያሉ ተቋራጮች ሥራውን በተሳካ ሁኔታ እንዲጨርሱ የማነሳሳት ሥራ ቢሰራም ያልተጨበጠ ተስፋ በመስጠት ቁርጠኝነቱ የሌላቸው መሆን፣በተጨማሪም ለፋብሪካው የመጡ ማቴሪያል ወደብ ደርሰው የጉምሩክ ግዴታ ተፈፅሞላቸው ስላልመጡ ምንም ማድረግ አይቻልም የሚል ምክንያቶች ማቅረብ የጊዜ መዘግየት እንዲደርስ የሆነ መሆኑን ገልፀው ፡-

1 ኛው ምዕራፍ የፋብሪካው ሥራ በተለያየ ፓኬጅ ብዙ ሥራዎች የሚቀሩት በመሆኑ የማጠናቀቂያ ሰርተፊኬት የማይሰጥ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

52. በተጨማሪም በአሰሪነት በኮርፖሬሽኑ የተመረጠው ተቋራጭ ኢፒሲ/EPC/ የፋይናንስ ችግር ያለበት በመሆኑ በስሩ ለሚሰሩ ተቋራጮች ክፍያ በወቅቱ ያለመክፈል ችግር ይታይበት የነበረ ሲሆን፣ እነዚህ በስሩ ያሉ ተቋራጮችም ለሥራ ብቁ ችሎታ ባለው የሰው ሃይል ያልተደራጁ የነበሩ በመሆኑ በሥራ ላይ የሥራ ማዘግየት የነበረ መሆኑን፣እንዲሁም የማሽነሪ ማስቀመጫ የሚሰራው ተቋራጭ ከ EPC ክፍያ በወቅቱ የማይደረግ በመሆኑ አብዛኛውን ጊዜ ጭቅጭቅ የነበረ በመሆኑ እነዚህ ምክንያቶች ለሥራው መዘግየት ከፍተኛ ጫና የፈጠሩ መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡

53. በስኳር ኮርፖሬሽን የፋብሪካ ግንባታ ዘርፍ ከተሰጠው ተግባር የፋብሪካ ግንባታ ፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ማስተባበር፣ መቆጣጠርና ማረጋገጥ ከመሆኑ አንፃር ያልተተገበረ በመሆኑ ሀገሪቷ ለሌላ ልማት ልታውለው የምትችለው ሀብት ለተጨማሪ ሥራ ትዕዛዝ እንዲውል አድርጓል፡፡





የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ እ.ኤ.አ ከሐምሌ 17/2009 እስከ እ.ኤ.አ ሰኔ 2016 ድረስ የመጀመሪያ ምዕራፍ 94.80% የደረሰ ሆኖ ሁለተኛው ምዕራፋ 31.39% ከማጠናቀቅያ ግዜ ለ 6 ዓመት በመዘግየት ሥራውን ያልጀመረ ፋብሪካን የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ፡፡

## ለመሬት ዝግጅትና ለሸንኮራ አገዳ ልማት የሚያስፈልጉ ግብዓትና

## አቅርቦት መሟላታቸውን በተለመከተ

54. ኮርፖሬሽኑ ለነበር ስኳር ፋብሪካዎች ማስፋፊያ ውጤታማነት፣ ለመሬት ዝግጅትና ለአገዳ ልማት የሚያስፈልጉ ግብዓትና ማሽነሪ አቅርቦት በሚፈለገው ጊዜ መሟላቱን ማረጋገጥና መደገፍ እንዲሁም የሸንኮራ አገዳ መሬት ዝግጅት ሥራ/Fine Level/ በታቀደ ጊዜና ወጪ መጠናቀቁን ሊከታታልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

55. ኮርፖሬሽኑ ለተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ውጤታማነት፣ ለመሬት ዝግጅትና ለአገዳ ልማት የሚያስፈልጉ ግብዓትና ማሽነሪ አቅርቦት በሚፈለገው ጊዜ መሟላቱን ያረጋገጠና የደገፈ፤እንዲሁም የሸንኮራ አገዳ መሬት ዝግጅት ሥራ/Fine level/ በታቀደ ጊዜና ወጪ መጠናቀቁን የተከታተለና የተቆጣጠረ፤እንዲሁም ድጋፍ ያደረገ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ በ 2007 በጀት ዓመት ለሸንኮራ አገዳ ልማት ለመሬት ዝግጅት እንዲውሉ የቀረቡ የማሽነሪ ሁኔታዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

| ተ.ቁ | የማሽን ዓይነት | አጠቃላይ ብዛት | በሥራ ላይ የዋሉ ማሽኖች ብዛት | ለጥገና የገቡ ማሽኖች ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ዶዘር | 23 | 6 | 17 |
| 2 | ጆንዲር | 5 | 3 | 2 |
| 3 | ቨርሳታይል | 10 | 6 | 4 |
| 4 | ኤስ.ቲ.ኤክስ 385 | 1 | - | 1 |
| 5 | ኤስ.ቲ.ኤክስ 380 | 5 | 2 | 3 |
| 6 | ኤስ.ቲ.ኤክስ 335 | 5 | 2 | 3 |
| 7 | ግሬደር ፓወር ፕለስ | 20 | 10 | 10 |
| 8 | ግሬደር ቸሪ | 9 | 2 | 7 |
| 9 | ግሬደር ኤክስ ሲ ኤም ጂ/XCMG/ | 1 | - | 1 |
| 10 | ኤም ኤክስ.ዩ 110 | 15 | 10 | 5 |
| 11 | ኤም ኤፍ 6495 | 14 | 8 | 6 |
| 12 | ካት 2204 | 4 | 1 | 3 |
| 13 | ዋይ ቲ ኦ/YTO/1804 | 5 | 3 | 2 |
| 14 | ዋይ ቲ ኦ/YTO/ 1304 | 1 | 1 | - |
| | ድምር | 118 | 54 | 64 |

ከሰንጠረዡ መረዳት እንደተቻለው በ 2007 በጀት ዓመት ለሸንኮራ አገዳ ልማት ዝግጅት እንዲውሉ የታቀዱ ማሽኖች ብዛታቸው 64/54.2%/የሚሆኑ በመለዋወጫ አቅርቦት ምክንያት ሥራ ላይ ባለመዋላቸው የግርድፍ እና የውሃ ገብ ርክክብ፣ የመሬት ድልዳሎና የአገዳ ተከላ ልማት እቅዶች አፈፃፀም ላይ ተፅዕኖ ያሳደሩ መሆኑ ታውቋል፡፡

56. ስለሁኔታው የተንዳሆ የእርሻ ዘርፍ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ማሽነሪዎች የሥራው አካል እንደመሆናቸው መጠን የሚያስፈልጋቸው የጥገና እና መለዋወጫ ፍላጎት ታሳቢ ተደርጎ በእቅድና በበጀት በዓመታዊ የፊዚካል እቅዱ አካል ሆነው የሚካተት ቢሆንም በራስ አቅም ለመጠገንም ይሁን በውጪ አካል እንዲጠገን/አውት ሶርስ/ ለማድረግ የሚያስችል መለዋወጫ በሚፈለገው ደረጃ በፋይናንስ በተደገፈ ሁኔታ የማይከናወን የነበረ በመሆኑ እና በሌላ በኩልም ለተጠቀሱት የመሬት ዝግጅት ማሽነሪዎች የሚያስፈልግ መለዋወጫ ከማፈላለግ ይልቅ ለኦፕሬሽን ትኩረት በመስጠት ለአገዳ ጫኝ ማሽኖችና አመላላሽ ትራክተሮች ትኩረት ይደረግ የነበረ በመሆኑ ችግሩ ያጋጠመ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

57. የስኳር ኮርፖሬሽን የፋብሪካ ግንባታና ኦፕሬሽን ዘርፍ ካለበት የሥራ ኃላፊነት አኳያ ዘመናዊ የማሽነሪዎች ጥገናና እድሳት አገልግሎት እንዲተገበር ድጋፍ ማድረግ ያለበት መሆኑን ከሚገልፀው አንፃር በወቅቱ ለሸንኮራ አገዳው ልማት የመሬት ዝግጅት ለሚያስፈልጉ ማሽነሪዎች ትኩረት ከመስጠት ይልቅ ለኦፕሬሽኑ ቅድሚያ በመስጠቱ በመለዋወጫ እጥረት ምክንያት ማሽነሪዎችን ሥራ ላይ እንዳይውሉ ባለማድረጉ ፋብሪካው በሚነሳበት ወቅት ከፍተኛ የሸንኮራ ግብዓት የሚጠይቅ በመሆኑ በአቅርቦት በኩል እጥረት እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡

## ዘመናዊ የማሽነሪዎች ጥገና እና እድሳት አገልግሎት መተግበሩን በተመለከተ

58. ኮርፖሬሽኑ ለስኳር ፋብሪካዎች ዘመናዊ የማሽነሪዎች ጥገና እና እድሳት አገልግሎት እንዲተገበር ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

59. ኮርፖሬሽኑ ለነባር ስኳር ፋብሪካዎች ዘመናዊ የማሽነሪዎች ጥገናና እድሳት አገልግሎት እንዲተገበር ድጋፍ ያደረገ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ በተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ በብልሽት ምክንያት አገልግሎት ሳይሰጡ የቆዩ በጋራዥ እና በፋብሪካው ቆመው የሚታዩ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

   1. ጆንዲር ግራፕ ሎደር ሞዴል 2254 መለያ ቁጥር 0009 የሆነ ከቀን 18/06/13 ጀምሮ በመንደር 6 በብልሽት ምክንያት ቆሞ የሚገኝ መሆኑ፣
   2. ኤም ኤክስ ዩ/MXU- 110/ መለያ ቁጥር 4047 የሆነ ከላዩ ተነስቶ ጊር ቦክሱና ኤንጅኑ ለጥገና ዱብቲ ጋራዥ ሚገኝ መሆኑ፣
   3. ኢት ኮድ 3- 27276 ከቀን 18/09/13 ጀምሮ እስከ ነሀሴ/2008 በኦዲቱ በአካል እስከ ታየ ድረስ በአሳይታ የተገኘ፣
   4. ሚስትቡሽ ሰሌዳ ቁጥሩ ኢት ኮድ 3- 38030 ከቀን 15/02/12 ጀምሮ በዱብቲ ጋራዥ አገልግሎት ባለመሰጠቱ በመስክ መሳሪያዎች ጥገና ቡድን ስር አሳይታ የሚገኝ መሆኑ ነሀሴ/2008 ዓ/ም በኦዲቱ አካል እይታ የታየ መሆኑ፤

5. የፋው ገልባጮች ሰሌዳ ቁጥር፡-ኢትኮድ 3- 53297 ከቀን 08/04/13 ጀምሮበመለዋወጫእጦት በዱብቲ ጋራዥቆሞ የሚገኝ መሆኑ፣

- ኢት ኮድ 3- 53378 ከቀን 23/06/13 ጀምሮ በመለዋወጫ እጦት በዱብቲ ጋራዥ ቆሞ የሚገኝ መሆኑ፣

6. ኤም ኤፍ/MF- 6495/ የሆነ ማሽነሪ መለያ ቁጥር 4041 ከቀን 04/12/12 ጀምሮ በዱብቲ ጋራዥ በመለዋወጫ እጦት ምክንያት ቆሞ የሚገኝ መሆኑ፣

7. የጆንዲር አርቲኩሌትድ ትራክተር ሞዴል 9410 መለያ ቁጥር 104 ከቀን 01/05/2013 ጀምሮ በመለዋወጫ እጥረት ምክንያት በዱብቲ ጋራዥ ቆሞ የሚገኝ መሆኑ፣

## በዴት ባህሪ ጋራዥ ቆመው የሚገኙ

1. ኤስቲኤክስ /STX- 380/ የመለያ ቁጥር 4005 የሆነ ማሽነሪ ከቀን 08/06/12 ጀምሮ በብልሽት ምክንያት አገልግሎት ሳይሰጥ በዴት ባህሪ የመስክ መሳሪያዎች ጥገና ጋራዥ የቆመ መሆኑ የታወቀ ቢሆንም፤ ከማሽነሪው ታሪክ 30/7/12 ቆሞ በ 7/3/13 ተነሳ እስከ 25/5/16 ሰርቶ ከዚህ ጀምሮ በመንደር 6 በጥገና ላይ የሚገኝ መሆኑ መታወቁ፣
2. ኤም ኤፍ/MF-6495/ መለያ ቁጥር 4033 ከቀን 08/06/12 በመለዋወጫ እጦት ችግር በዴት ባህሪ ጋዥ የሚገኝ መሆኑ፣
3. የሻንቱ ቡልዶዘር SD 22 መለያ ቁጥር 0001 ከቀን 21/07/2013 ጀምሮ በመንደር 6 እና 0002 ከቀን 25/07/2013 ጀምሮ በመንደር 4 በመለዋወጫ እጦት ምክንያት ቆመው የሚገኙ መሆኑ፣
4. 05-400117 ዋይ ቲኦ/YTO 1804/ በመለዋወጫ ችግር ምክንያት በዴት ባህሪ ቆሞ የሚገኝ፣
5. ማሲ ፈርግሰን/Massey Fergsan/ 05-4040 በሶፍት ዌር/RPM/ ችግር ምክንያት በዴት ባህሪ ጋራዥ ችግር የቆመ፣
6. 05-400125 ዋይቲኦ/YTO/ በትራንስሚሽን ችግር ምክንያት በዴት ባህሪ ጋራዥ ቆሞ የሚገኝ መሆኑ ታውቋል፡፡

60. ስለ ሁኔታው በተንዳሆ ጋራዥ ሱፐርቫይዘር እና ሊድ መካኒክ ኃላፊዎች የኦዲት ቡድኑ በአካል እይታ እና በቃለ-መጠይቅ ላቀረበላቸው ጥያቄዎች በሰጡት መልስ በዱብቲ፣ በመንደር 6፣ በመንደር 4 እና በዴት ባህሪ ጋራዥ በመለዋወጫ ችግር ምክንያት ቆመው የሚገኙ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

61. ኮርፖሬሽኑ ከላይ ለተዘረዘሩት ማሽነሪዎችና ተሽከርካሪዎች የመለዋወጫ ድጋፍ በማድረግ የሚጠበቅባቸውን አገልግሎት እንዳይወጡ ያደረገ በመሆኑ በሸንኮራ አገዳ እርሻ ልማቱ ዓመታዊ እቅድ አፈፃፀም ላይ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡











በተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ በመለዋወጫ ችግር ምክንያት የቆሙ ማሽነሪዎችና ተሽከርካሪዎችን የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ፡፡

## በቴክኖሎጂ በመደገፍ የሸንኮራ አገዳ ልማት ምርታማነት መሻሻሉን በተመለከተ

62. ኮርፖሬሽኑ የነበር ስኳር ፋብሪካዎች ማስፋፊያዎችን የእርሻ ኦፕሬሽን በመከታተል፣ በመቆጣጠር እና በቴክኖሎጂ በመደገፍ የሸንኮራ አገዳ አማካይ ምርታማነትን 9.5 ቶን በሄክታር በወር መድረሱን፤ እንዲሁም የሸንኮራ አገዳ የስኳር ይዘት 13.48% መድረሱን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

63. ኮርፖሬሽኑ የነባር ስኳር ፋብሪካዎች ማስፋፊያ የእርሻ ኦፕሬሽን በመከታተል፣በመቆጣጠርና በቴክኖሎጂ በመደገፍ የሸንኮራ አገዳ አማካይ ምርታማነትን 9.5 ቶን በሄክታር በወር የደረሰ መሆኑን፤እንዲሁም የሸንኮራ አገዳ የስኳር ይዘት 13.48% መሆኑን ያረጋጋጠ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፣ በተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ የሸንኮራ አገዳ ተከላ ሥራ በ2006 በጀት ዓመት 16,882 ሄክታር ለመትከል ታቅዶ ክንውኑ 6,953.70/41.19%/ መሆኑ እና በ 2007 በጀት ዓመት 10,521 ሄክታር ለመትከል ታቅዶ አፈፃፀሙ 1,316/12.51%/ ሄክታር በመሆኑ የሁለቱም በጀት ዓመት አፈፃፀም ዝቅተኛ አፈፃፀም የሚያሳይ በመሆኑ የሸንኮራ አገዳ አማካይ ምርታማነት 9.5 ቶን በሄክታር በወር መድረሱን የማያመለክት ሲሆን፤ የስኳር ይዘቱ 13.48 % ስለመድረሱ በኦዲቱ ወቅት ፋብሪካው በምርት ሂደት ላይ ባለመሆኑ ማወቅ ያልተቻለ መሆኑ ታውቋል፡፡

64. ስለ ሁኔታው በኦዲት ቡድኑ ለእርሻ ኦፕሬሽን ዘርፍ ኃላፊዎች ለቀረበ ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ አገዳ በባህሪው ቅድመ ዘር ማሳ ዝግጅት አንድ ዓመት፣ የዘር ማሳ ዝግጅት አንድ ዓመት እንዲሁም የኮሜርሻል አገዳ ተተክሎ ፋብሪካ እስከሚገባ ድረስ በተንዳሆ ነባራዊ ሁኔታ ከ 12 ወራት እስከ 14 ወራት የሚፈልግ ሲሆን በአጠቃላይ አገዳ ከመጀመሪው ሂደት ፋብሪካ ለመፈጨት እስከሚገባ ድረስ 3 ዓመት የሚያስፈልግ መሆኑን ገልፀው የአገዳ ልማት ግርድፍ እና ውሃ ገብ መሬት ርክክብ ከውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ሥራ አፈፃፀም ጋር የተያያዘ በመሆን እና በራስ በኩል የሚያስፈልጉ ማሽነሪዎችን ዝግጁ በማድረግ በኩል የመለዋወጫ ችግር በመኖሩ አፈፃፀሙን ዝቅ ሊያደርግ መቻሉን ገልፀዋል፡፡

65. በስኳር ኮርፖሬሽን የእርሻ ኦፐሬሽን ክትትል፣ድጋፍና ቁጥጥር ከተሰጠው የሥራ ድርሻ በእርሻና በፋብሪካ ኦፕሬሽን ያለውን ቅንጅት/Synchronization/ መከታተል፣ መቆጣጠርና ማረጋገጥ ከመሆኑ አንፃር የክትትል ሥራ ያልተሰራ በመሆኑ ለአገዳ ልማት እርሻ የሚሆኑ ማሳዎች ለማሽነሪ የሚሆኑ መለዋወጫዎች ባለመቅረባቸው ዓመታዊ የመሬት ዝግጅት እቅድ ግቦች እንዳይሳኩ ያደረገ ሲሆን፤ የስኳር ፋብሪካዎቹም በታቀደላቸው ጊዜ አለመጠናቀቅ በለሙ ማሳዎች ያሉ አገዳዎች እንዲወገዱ በመደረጉ ለልማቱ የወጣውን ሀብት እንዲባክን አድርጓል፡፡

## ግዥዎች ግልፅነትና ተጠያቂነት ባለበት ሁኔታ የሚፈፀሙ መሆኑን በተመለከተ

66. ኮርፖሬሽኑ ለነባር ስኳር ፋብሪካዎች ማስፋፊያ ውጤታማነት ግዥዎችን ግልፅነትና ተጠያቂነት ባለበት እንዲሁም ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ በአግባቡ ሊፈፅም ይገባል፡፡

67. ኮርፖሬሽኑ ለነባር ስኳር ፋብሪካዎች ማስፋፊያው ጤታማነት ግዥዎችን ግልፅነትና ተጠያቂነት ባለበት፤እንዲሁም ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ መፈፀማቸውን ክትትልና ቁጥጥር ያደረገ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ በተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ለሰራተኞች መኖሪያ የተሰሩ ብዛታቸው 499 የሆኑ ግንባታቸው ከ300 በላይ ተቋራጮች/ኮንትራክተሮች/ በኮንትራትውል/በማስረጃነት ባልቀረበ/ መሰረት ከሀምሌ 2001 ዓ.ም ጀምሮ ብዙዎቹ በተለያየ ቀን መፈረማቸው የተገለፀ፤እንዲሁም የሥራ ማጠናቀቂያ ጊዜያቸው እንደ ህንፃው ዓይነትየሆነበ 10 ወር፣በ 6 ወር፣በ 4 ወር፣በ 3 ወርየሆነየግንባታ ሥራውን የወሰዱት በጨረታ ስለ መሆኑ ማስረጃ የሌለ በመሆኑ ማወቅ አለመቻሉ ታውቋል፡፡

68. እንዲሁም ተቋራጮቹም ሆነ አማካሪ የቤቶቹን ግንባታ ለመሥራትም ሆነ የምክር አገልግሎት ለመስጠት በምን ያህል ዋጋ ሥራ እንደ ጀመሩና መቼ ለማጠናቀቅ ውል እንደ ገቡ የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ ያልተቻለ መሆኑ ታውቋል፡፡

69. በተጨማሪም ከተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ 2006/07 በጀት ዓመት የውስጥ ኦዲት ሪፖርት መረዳት እንደተቻለው ለማሳያ እንደሚከተለው ቀርቧል፡
   - የመስክ መሳሪያ ጥገና ቡድን የጥገና አገልግሎት ለመስጠት በቂ መሳሪዎችና አገልግሎት የሌለው በመሆኑ መሳሪያዎችና ተሽከርካሪዎች ተጠግነው ወደ ሥራ ሳይገቡ ለረጅም ጊዜ የሚቆሙ መሆኑ፣
   - በመለዋወጫ እጦት ምክንያት በኪራይ ተሽከርካሪዎችና እና ማሽነሪዎች ፋብሪካው ለወጪ መዳረጉ ሲሆን፤የመለዋወጫው ችግር አሁንም ያለ ችግር መሆኑ ታውቋል፡፡

70. በ2005/2006 በጀት ዓመት በውስጥ ኦዲት ሪፖርት በተገኘ መረጃ መሰረት ከብረታብረት ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን ለማሽነሪ ብር 44 ሚሊዮን የግዥ ውል ተፈፅሞ ከውለታው ቀን በላይ አንድ ዓመት መዘግየቱ ተመልክቷል፡፡

71. ስለ ሁኔታው በኦዲት ቡድኑ ለተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ወኪል የህንፃ ግንባታና ጥገና ቡድን መሪ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ ማስረጃ ስለሌለ ማወቅ ያልቻሉ መሆኑን ሲገልፁ የመለዋወጫ ችግርን በተመለከተ የውስጥ ኦዲት ቡድኑ ያልተፈታ ችግር መሆኑን ሲገልፁ ከብረታብረት ኢንጅነሪንግ ጋር ስለተፈፀመ ውል መልስ የሰጠ አካል የለም፡፡

72. 499 የመኖሪያ ቤት ግንባታዎች ብዛት ላላቸው ከ 300 በላይ ተቋራጮች በውል ባልታሰረ ሁኔታ እንዲሰሩ ማድረግ እና አስፈላጊ መለዋወጫዎችን በማቅራብ ራስን በመቻል መሳሪያዎችና ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልግሎት ላይ እንዲውሉ አለማድረግ እና በኪራይ መጠቀም ስኳር ፋብሪካውን ለብልሹ አሰራር ተጋላጭ እንዲሆን የሚዳርግ ይሆናል፡፡

## ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ቋሚ ንብረቶች በኮርፖሬሽኑ መመሪያ መሰረት የሚወገዱ መሆኑን በተመለከተ

73. በእርጅና እና በተለያዩ ምክንያቶች ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ የስኳር ፋብሪካ ቋሚ ንብረቶች በኮርፖሬሽኑ የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት በአስወጋጅ ኮሚቴ ተጣርተው ለውሳኔ ቀርበው እንዲወገዱ ሊደረግ ይገባል፡፡

74. ኮርፖሬሽኑ በእርጅና እና በተለያዩ ምክንያቶች ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ የነባር ስኳር ማስፋፊያ ፋብሪካዎች ቋሚ ንብረቶች በኮርፖሬሽኑ የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት በአስወጋጅ ኮሚቴ ተጣርተው ለውሳኔ ቀርበው እንዲወገዱ ክትትል ያደረገ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ በተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ጥቅም ላይ የማይውሉ ናቸው የተባሉ እና መወገድ ሲገባቸው ያልተወገዱ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

    1. ፎርድ ሬንጀር ፒክ-አፕ/Ford Ranger Pick-up/ የሰሌዳ ቁጥር ኢ.ት ኮድ 3-27281 ከቀን እ.ኤ.አ 10/06/12 እና ኢ.ት ኮድ 3-27279 እ.ኤ.አ ከቀን 26/02/13 ከጥቅም ውጪ የሆኑ በዱብቲ ጋራዥ የሚገኙ መሆኑ፣
    2. ኒሳን ሰሎዳ ቁጥር ኢ.ት ኮድ 3- 40415 ከቀን 12/08/13 ጀምሮ ከጥቅም ውጪ የሆነ በዱብቲ ጋራዥ የሚገኝ፣
    3. ሳሚ/SAME- 130/ መለያ ቁጥር 520 ከጥቅም ውጪ ሆኖ ዱብቲ ጋራዥ የሚገኝ፣
    4. ግሬደር ኮሚያስ/ Grader KOMAIS- 0069 / ጥቅም ላይ የማይውል በዱብቲ ጋራዥ የሚገኝ፣
    5. ግሬደር ካተር ፒላር /Grader Caterpillar/ ጥቅም ላይ የማይውል በዱብቲ ጋራዥ የሚገኝ፣
    6. ኤክስካቫት ፊያታሊስ/Excavat Fiatallis F.A 009/ በዱብቲ ጋራዥ ከጥቅም ውጪ ሆኖ የሚገኝ፣
    7. ሜርሰዲስ/Mercedes/ ኢ.ት ኮድ 3- 13038 ከጥቅም ውጪ ሆኖ በዱብቲ ጋራዥ የቆመ፣
    8. ቶዮታ ላንድ ክሩዘር/Toyota Land Crusier/ ኢ.ት ኮድ 3- 15917 በዱብቲ ጋራዥ ከጥቅም ውጪ ሆኖ የሚገኝ፣
    9. ፊያት ኤን ሶስት/ Fiat N3/ ኢ.ት ኮድ 3-15919 ከጥቅም ውጪ በዲብቲ ጋራዥ የሚገኝ፣
    10. ኤም ኤፍ/ MF 290/ መለያ ቁጥር 0516 በዴት ባህሪ ከጥቅም ውጪ ሆኖ የቆመ፣

11. ሳሚ/SAME-130/ መለያ ቁጥር 524 በዴት ባህሪ ከጥቅም ውጪ ሆኖ የቆመ፣

12. ኤሌተር /Elleter/ ገልባጭ የሰሌዳ ቁጥር ኢ.ት ኮድ 3-15923 በዴት ባህሪ ከጥቅም ውጪ ሆኖ የሚገኝ፣ በድምር 13 የሆኑ ቀላል እና ከባድ ተሽከርካሪዎችና ማሽነሪዎች በኮርፖሬሽኑ የንብረት አስተዳደር መመሪያ አንቀጽ 26 መሰረት ያልተወገዱ መሆኑ ታውቋል፡፡

75. ስለሁኔታው በኦዲት ቡድኑ በመስክ እይታ ወቅት ለተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ጋራዥ ሱፐር ቫይዘር እና ለሲድ ሜካኒክ ላቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ከላይ በዝርዝር የተገለፁት 13 የሆኑ ቀላል እና ከባድ ተሽከርካሪዎችና ማሽነሪዎች ለፋብሪካው ጥቅም ላይ የማይውሉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

76. በኮርፖሬሽኑ መመሪያ መሰረት ለሌላ አካል ሥራ ላይ ሊውሉ የሚችሉ ቋሚ ንብረቶችአለመወገዳቸው ጋራዦች ያላቸውን ቦታ ከማጣበባቸውም በላይ ፋብሪካው ተጨማሪ ገቢ እንዳያገኝ ያደርጋል፡፡

## ምርምርና ስልጠና የተሻሻለ የሸንኮራ አገዳ እና ስኳር አመራረት ቴክኖሎጂን መጠቀሙን በተመለከተ

77. ምርምርና ስልጠና የተሻሻለ የሸንኮራ አገዳ እና ስኳር አመራረት ቴክኖሎጂ በማውጣት የፋብሪካዎች ተወዳዳሪነት እንዲጎለብት ሊያደርግ ይገባል፡፡

78. ኮርፖሬሽኑ በምርምርና ስልጠና የተሻሻለ የሸንኮራ አገዳ እና ስኳር አመራረት ቴክኖሎጂ በማውጣት የፋብሪካዎችን ተወዳዳሪነት እንዲጎለብት ያደረገ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ በተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ የሸንኮራ አገዳ ልማትን ምርታማነት ከመጨመር አንፃር የአካባቢውን የአየር ንብረት / ስነ-ምህዳርና የአፈር ሁኔታ ያገናዘበ በመስኖ ውሃ መርሃ-ግብር/ መጠቀም፣ ከዘር ጥራት፣ብቅለትና መቋቋም አንፃር መስራች የዘር አገዳ/ቲሹ ከልቸር/ችግኞች ማስገባትና ጥቅም ላይ እንዲውሉ የማድረግ ሥራ እየተሰራ መሆኑ በተንዳሆ እርሻ ምርምር ጣቢያ ቢገለፅም፣ ኮርፖሬሽኑ ለተንዳሆ ሸንኮራ አገዳ ልማት ሥራ የቲሹ ከልቸርን ሥራ ላይ ለማዋል ምን ያህል በጀት እንደተመደበ እና ወጪ እንዳወጣ ማወቅ ያልተቻለ መሆኑ ታውቋል::

79. በተጨማሪም የተንዳሆ እርሻ ምርምር እና ስልጠና ጣቢያ በተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ምርት ማምረት አለመጀመር ምክንያት የቆረጣ ጊዜ ያለፈባቸው የሸንኮራ አገዳ በ 2008 በጀት ዓመት 303.17 ሄክታር ጥቅም ላይ የማይውሉ ተብሎ እንዲገለበጥ የተደረጉ መሆኑ ታውቋል፡፡

80. ከ2006/07 በጀት ዓመት እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት መረዳት እንደተቻለው በተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ በአገዳ እድሜ እርጅና ምክንያት የአገዳ የስኩሮዝ ይዘቱ እጅግ አነስተኛ በመሆኑ በፋብሪካው አገዳ መፍጨት ሂደት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ በማሳደሩ 1,340.9 ሄክታር የአገዳ ማሳ ሙሉ ለሙሉ የተወገደ መሆኑ ታውቋል፡፡

81. በስኳር ኮርፖሬሽን ምርምርና ስልጠና ዘርፍ እድሜው የገፋ አገዳ አያያዝና አጠቃቀም ምክረ-ሀሳብ ህዳር/2008 ዓ.ም በተሰጠ ስልጠና በኢትዮጵያ የአገዳ መቁረጫ እድሜ ከ 12- 24 ወር በመሆኑ ከዚህ ካለፈ የስኳር ምርቱ የሚቀንስ መሆኑ ቢገለፅም፤ ፋብሪካው አገዳውን ተቀብሎ ባለመፍጨቱ ምክንያት 800 ሄክታር እድሜው በገፋ አገዳ መሸፈኑ ታውቋል፡፡

82. ስለ ሁኔታው የተንዳሆ ምርምር ጣቢያ ቡድን መሪ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ የቆረጣ ጊዜያቸው ያለፈባቸው አገዳዎች በየጊዜው የአገዳ ስኳር ጥራት እየተፈተሸና የአገዳ ሽፋናቸው የደረሰበት ደረጃ እየታየ እራሳቸውን ችለው አልያም ከሌሎች አገዳዎች ተቀይጠው ወደ ፋብሪካ መሄድ እስከሚችሉበት ደረጃ ባሉበት እንክብካቤ እየተደረገላቸው እንዲቆዩ የሚደረግ ሲሆን ከዚህ ውጪ ከሆኑ ጉቶአቸው/ራቱናቸው/ የሚቀጥሉበት ሁኔታ ታይቶ ይቀጥሉ የሚባሉት የሚቀጥሉ ሲሆን እንዳይቀጥሉ የተወሰነባቸው ተገልብጠው የእርሻ ማሳዎቹ ለአዲስ ተከላ እንዲዘጋጁ የሚደረግ በመሆኑ በ 2008 በጀት ዓ.ም 303.17 ሄክታር እንዲገለበጡ ሲደረግ 259.5 ሄክታር ጉቶአቸው/ራቱናቸው/ ያልተጎዳ በመሆኑ በዘርነት እንዲቀጥሉ የተደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

83. በተጨማሪም የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ የእርሻ ዘርፍ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ እ.ኤ.አ ሰኔ 2011 የመጀመሪያው ምዕራፍ ፋብሪካ ኮሚሽን እንደሚደረግ እና እ.ኤ.አ ጥቅምት 2011 የማምረት ሥራውን እንደሚጀምር፣ እንዲሁም እ.ኤ.አ ከታህሳስ 2009 እስከ እ.ኤ.አ ሰኔ 2012 የሁለተኛ ምዕራፍ ፋብሪካ ኮሚሽን እንደሚደረግ እና እ.ኤ.አ ጥቅምት 2012 የሙከራ ምርት ሥራ እንደሚጀምር እቅድ የተያዘ ሆኖ ባለመፈፀሙና እቅዱ እየተከለሰ የቆየ በመሆኑ በተለይም ፒሲ 1፣ ፒሲ 2 እና 3 የአገዳ ማሳዎች ከ 2 እና ከ 3 ጊዜ በላይ እድሜው የገፋ አገዳ 1,340.9 ሄክታር በ 2007 በጀት ዓ.ም እንዲወገድ ተደርጉ ጉቶአቸው/ራቱን/ እንዲቀጥል የተደረገ መሆኑን ገልፀው የሸንኮራ አገዳ እድሜው ከገፋ የስኩሮዝ/ጁስ/ ይዘቱ የሚቀንስ መሆኑን አመልክተው የአገዳው መወገድ ሶስት መሰረታዊ ጥቅሞች እንደሚኖሩትም እንደሚከተለው አብራርተዋል፡፡

- እድሜው የገፋ አገዳ እንዲወገድ ቢደረግም ከስር ያለው ጉቶው/ራቱን/ እንዲቀጥል የሚደረግ በመሆኑ የተሻለ ምርት ለቀጣይ ምርት ወቅት የሚሰጥ መሆኑ፣
- የሚወገደው አገዳ ለሰራተኞች እህል ማብሰያ የሚጠቅም በመሆኑ፣
- ለአካባቢው ማህበረሰብ እንስሳቶች ከማሳ ውጪ ራቅ ተደርጎ በማራገፍ ለመኖነት የሚውል መሆኑን ገልፀዋል፡፡

84. በስኳር ኮርፖሬሽን የፋብሪካ ግንባታና ኦፕሬሽን ከተሰጠው ተግባር በሀገር በቀል አቅም አስተማማኝ አዋጭ የሆነ የፋብሪካ ግንባታና ኮሚሽኒንግ ሥራ ማከናወን ከሚለው አንፃር የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ክትትል ያልተደረገለት በመሆኑ ሰባት ዓመታት መጠናቀቅ ከሚገባው ጊዜ በማሳለፉ ለፋብሪካው ሊውል የሚችል ግብዓት የሀገር ሀብት ወጪ የተደረገለት ጥቅም ላይ ሳይውል ከፍተኛ ወጪ እንዲባክን ሆኗል፡፡

## የአካባቢ ጥበቃ እንክብካቤን በተመለከተ

85. ማንኛውም ፕሮጀክት የአካባቢ ጥበቃ ተፅዕኖ ግምገማ ተደርጎለት የአካባቢ ጥበቃ ተፅዕኖ ስለማስከተሉ ወይም አለማስከተሉ ተለይቶ እንዲታወቅ ሊደረግ ይገባል፡፡

86. ኮርፖሬሽኑ ከስኳር ፋብሪካዎች ማስፋፊያ ሥራ ጋር የአካባቢ ጥበቃ እንክብካቤ መሰራቱን ክትትል ያደረገ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፡-በተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ይዞታ ስር ከሚገኙት 11 መንደሮችውስጥ 9 መንደሮች ውስጥ ለሰራተኛው መኖሪያነት ውብና ምቹ ከማድረግ አኳያ ከአካባቢው የአየር ንብረት ጋር የሚጣጣም ሀገር በቀል ችግኞችን በመትከል የፀዳ አካባቢ መፍጠር የሚያስችል ሥራ መሰራቱ ቢታወቅም፣መንደር 18 ተብሎ የሚጠራው አሳይታ የሚገኘው የአብዛኛው ሰራተኛ መኖሪያ የአካባቢውን ሞቃት ንፋስና ሙቀት መቀነስ የሚችል የዛፍ ዓይነት የማይታይበት መሆኑ በአካል ማየት ተችሏል፡፡

87. በተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ የአካባቢ ጥበቃን ለሚመለከት ባለሙያ በኦዲት ቡዱኑ ለቀረበ ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ ሰራተኞች ከሚኖሩባቸው 11 መንደሮች ውስጥ በ 9 ኙ ምቹ የሰራተኛ መኖሪያ ተፈጠረ መሆኑ ሲገለፅ ሁለቱ ገና መሆናቸውን አመልክቷል፡፡

88. የኦዲት ቡድኑ በአካል በመንደር 18 አብዛኛው ሰራተኛ የሚኖር መሆኑን፣ እንዲሁም የችግሩ ተካፋይ በመሆን የተመለከተ በመሆኑ  መንደሩ እጅግ ሞቃታማ በመሆኑ ወደ አረንጓዴነት በእፅዋት እንዲቀየር ባለመደረጉ ከአየር ሁኔታ ጋር በተገናዘበ የሰራተኛ መልቀቅ እንዲከሰት ያደርጋል፡፡

# ክፍል ሶስት
# የመደምደሚያ ሀሳቦች

ከላይ በኦዲት ግኝቶቹ ላይ እንደተመለከተው በስኳር ኮርፖሬሽን የነባር ስኳር ፋብሪካዎች የማስፋፊያ ሥራዎች አፈፃፀም እና ውጤታማነትን በተመለተ በስኳር ኮርፖሬሽን እና በናሙና በኦዲቱ ተመርጦ በታየው በተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ማስፋፊያ የታዩ ግኝቶች ላይ የሚከተሉት መደምደሚያ ሀሳቦች ላይ ተደርሷል፡፡

89. ኮርፖሬሽኑ አስተማማኝና አዋጭ የሆነ የጨረታ ሂደት እና ድርድር ባለመተግበር የስኳር ፋብሪካ ግንባታና ተከላውን በተናጠል ፓኬጅ አወዳድሮ በጨረታ ሂደቱ ወቅት ለተጫራቾች ባልተገለፀ ውሳኔ ከመሀል አንድ መርጦ በመሾም ሌሎቻችሁ በተመረጠው ስር ሆናችሁ ስሩ በሚል ሂደት ለማሰራት በመሞከሩ ወደ ክስ ሂደት በማድረሱ በፋብሪካው የሥራ ሂደት ላይ የጊዜ መጓተት ብክነት እንዲኖር ማድረጉ፣

90. በስኳር ኮርፖሬሽን የኮርፖሬት እቅድና ግምገማ ዘርፍ ከተሰጠው ተግባር ኮርፖሬሽኑ በወቅቱና በጥራት የተዘጋጀ መሪ እቅድ፣ እስትራቴጂክ እቅድ፣ የኦፕሬሽን እቅድና በጀት እንዲኖር፣ የእቅድ አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ በወቅቱ እንዲከናወን እና በማኔጅመንት የሚሰጡ ግብረ መልሶችና ውሳኔዎች ትግበራ እንዲሆኑ እና የፕሮጀክት ሥራዎች ተቀናጅተው እንዲሰሩና የተቀመጡት ግቦች እንዲሳኩ ከሚለው አኳያ ተግባራዊ ያልተደረገ በመሆኑ በተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ የታቀዱ እቅዶች በኮርፖሬሽኑ እና በስኳር ፋብሪካው በቅንጅታዊ አሰራር ሀብት/ሪሶርስ/ አጠቃቀም ምክንያት በተፈጠሩ ችግሮች ዓመታዊ የግርድፍ መሬት፣ውሃ ገብ መሬት ርክክብና የአገዳ ተከላ እቅዶች ያልተሳኩ መሆኑ፣

91. በስኳር ኮርፖሬሽን የፋብሪካና ኦፕሬሽን ዘርፍ ከተሰጠው ተግባር አስተማማኝና አዋጭ የቴክኖሎጂ መረጣ ማድረግ እና በሀገር በቀል አቅም አስተማማኝና አዋጭ የሆነ የፋብሪካ ግንባታና ኮሚሽኒንግ ሥራ ማከናወን ከሚለው አንፃር ክትትል ባለመደረጉ የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ግንባታና ተከላ እ.ኤ.አ ከ ሐምሌ 17/2009 እስከ እ.ኤ.አ ሰኔ 2016 ድረስ የመጀመሪው ምዕራፍ 94.80% የደረሰ ሆኖ ሁለተኛው ምዕራፍ 31.39%/ ከማጠናቀቂያ ጊዜ ለ 4 ዓመት በመዘግየት/፤ የእርሻ ዘርፍ አፈፃፀምም አለመሳከትና በቤቶች ግንባታም ለ 469 ቤቶች 300 ተቋራጮች በውል ባልታሰረ ሁኔታ ሥራ ማሰራት በኮርፖሬሽኑ የክትትልና ቁጥጥር ስርዓት እጅግ የላላ መሆኑን የሚያመለክት መሆኑ፣

92. በስኳር ኮርፖሬሽን የፋብሪካ ግንባታ ዘርፍ ከተሰጠው ተግባር የፋብሪካ ግንባታ ፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ማስተባበር፣ መቆጣጠርና ማረጋገጥ ከሚለው አንፃር ያልተተገበረ በመሆኑ የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ግንባታና ተከላ በታቀደለት ጊዜና በተመደበለት ወጪ ባለማጠናቀቁ ሀገሪቷ ለሌላ ልማት ልታውለው የምትችለው ሀብት ለተጨማሪ ሥራ ትዕዛዝ እንዲውል መደረጉ፣

93. የስኳር ኮርፖሬሽን የፋብሪካ ግንባታና ኦፕሬሽን ዘርፍ ካለበት የሥራ ኃላፊነት አኳያ ዘመናዊ የማሽነሪዎች ጥገናና እድሳት አገልግሎት እንዲተገበር ድጋፍ ማድረግ ያለበት መሆኑን ከሚገልፀው አንፃር በወቅቱ ለተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ለሸንኮራ አገዳ ልማት የመሬት ዝግጅት ለሚያስፈልጉ ማሽነሪዎች  መለዋወጫ ባለማቅረቡ  ሥራ ላይ እንዳይውሉ መደረጉ፣

94. ኮርፖሬሽኑ ለስኳር ፋብሪካዎች ዘመናዊ የማሽነሪዎች ጥገና እና እድሳት አገልግሎት እንዲተገበር የመለዋወጫ ድጋፍ በማድረግ ማሽነሪዎች የሚጠበቅባቸውን ሥራ እንዳይሰሩ ያደረገ በመሆኑ በሸንኮራ አገዳ እርሻ ልማቱ ዓመታዊ እቅድ አፈፃፀም ላይ ተፅኖ ማሳደሩ፣

95. በስኳር ኮርፖሬሽን የእርሻ ኦፕሬሽን ክትትል፣ድጋፍና ቁጥጥር ከተሰጠው የሥራ ድርሻ በእርሻና በፋብሪካ ኦፕሬሽን ያለውን ቅንጅት/Synchronization/ መከታተል፣ መቆጣጠርና ማረጋገጥ የሚል ቢሆንም፤ ከዚህ አንፃር የክትትል ሥራ ያልተሰራ በመሆኑ ለአገዳ ልማት እርሻ የሚሆኑ ማሳዎች እና ለማሽነሪ የሚሆኑ መለዋወጫዎች ባለመቅረባቸው ዓመታዊ የመሬት ዝግጅት ግቦች እንዳይሳኩ ያደረገ ሲሆን፤ የስኳር ፋብሪካዎቹም በታቀደላቸው ጊዜ አለመጠናቀቅ በለሙ ማሳዎች ያሉ አገዳዎች እንዲወገዱ ምክንያት በመሆኑ በ ለልማቱ የወጣውን ሀብት እንዲባክን ማድረጉ፣

96. በተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ 499 የመኖሪያ ቤት ግንባታዎች እጅግ ብዛት ላላቸው 300 ተቋራጮች በውል ባልታሰረ ሁኔታ እንዲሰሩ መደረጉ እና አስፈላጊ መለዋወጫዎችን በማቅራብ ራስን በመቻል የጥገናና የእድሳት አገልግሎት አለማድረግ እና በኪራይ ማሽነሪዎችን መጠቀም ስኳር ፋብሪካውን ላልተገባ ወጪ የሚዳርግ መሆኑ፣

97. በእርጅናና በተለያ ምክንያቶች ጥቅም ላይ የማይውሉ ቋሚ ንብረቶች  በኮርፖሬሽኑ መመሪያ መሰረት  ለሌላ አካል ሥራ ላይ ሊውሉ የሚችሉ  አለመወገዳቸው ጋራገሮች ያላቸውን ቦታ ከማጣበባቸውም በላይ ፋብሪካው ተጨማሪ ገቢ እንዳያገኝ ያደረጉ መሆኑ፣

98. በስኳር ኮርፖሬሽን የፋብሪካ ግንባታና ኦፕሬሽን ከተሰጠው ተግባር በሀገር በቀል አቅም አስተማማኝ አዋጭ የሆነ የፋብሪካ ግንባታና ኮሚሽኒንግ ሥራ ማከናወን ከሚለው አንፃር የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ክትትል ያልተደረገለት በመሆኑ ሰባት ዓመታት መጠናቀቅ ከሚገባው ጊዜ በማሳለፉ ለፋብሪካው ሊውል የሚችል ግብዓት የሸንኮራ አገዳ በ 2007 በጀት ዓመት 1340.9 ሄክታር እንዲሁም በ 2008 በጀት ዓመት 303.17 ሄክታር የአገዳ ማሳዎች የሀገር ሀብት ወጪ የተደረገባቸው ጥቅም ላይ ሳይውሉ  እንዲገለበጡ መደረጉ፣

99. የአካባቢ ጥበቃ እንክብካቤን በተመለከተ በተንዳሆ በመንደር 18 አብዛኛው ሰራተኛ የሚኖር መሆኑ  መንደሩ እጅግ ሞቃታማ በመሆኑ እና ወደ አረንጓዴነት በእፅዋት እንዲቀየር ባለመደረጉ ከአየር ሁኔታ ጋር በተገናዘበ የሰራተኛ መልቀቅ የሚያስከትል መሆኑ፣

## ክፍል አራት
## የማሻሻያሀሳቦች

100.ኮርፖሬሽኑ አስተማማኝና አዋጭ የሆነ የጨረታ ሂደት እና ድርድር ሊያከናውን ይገባል፡፡

101.ኮርፖሬሽኑ በወቅቱና በጥራት የኦፕሬሽን እቅድና በጀት እንዲኖር፣ የእቅድ አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ በወቅቱ እንዲከናወን እና በማኔጅመንት የሚሰጡ ግብረ መልሶችና ውሳኔዎች ትግበራ እንዲሆኑ እና የፕሮጀክት ሥራዎች ተቀናጅተው እንዲሰሩና የተቀመጡት ግቦች እንዲሳኩ ሊያደርግ ይገባል፡፡

102.ኮርፖሬሽኑ አስተማማኝና አዋጭ የቴክኖሎጂ መረጣ ሊያደርግ እና የፋብሪካ ግንባታና ኮሚሽኒንግ ሥራ በወቅተ እንዲከናወን፣እንዲሁም የሰራተኛ መኖሪያ ቤት ግንባታ ሥራ የሚወስዱ ተቋራጮችን በውል በታሰረ ሁኔታ ሊያሰራ ይገባል፡፤

103.ኮርፖሬሽኑ የፋብሪካ ግንባታ ፕሮጀክቶችን አፈፃፀም በታቀደለ ጊዜና በተመደበ ወጪ እንዲጠናቀቁ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

104.ኮርፖሬሽኑ ዘመናዊ የማሽነሪዎች ጥገናና እድሳት አገልግሎት እንዲተገበር ድጋፍ በማድረግ የሸንኮራ አገዳ እርሻ ልማቱ ዓመታዊ እቅድ አፈፃፀም የተሳካ እንዲሆን ሊያደርግ ይገባል፡፡

105.ኮርፖሬሽኑ የስኳር ፋብሪካዎች በታቀደላቸው ጊዜ ተጠናቀው የሙከራ ፍተሻ/ኮሚሽኒንግ/ እንዲደረግላቸው በማድረግ በለሙ ማሳዎች ያሉ አገዳዎች ጊዜ አልፎባቸው ከጥቅም ውጪ ሳይሆኑ ሥራ ላይ እንዲውሉ ሊያስደርግ ይገባል፡፡

106.ኮርፖሬሽኑ አስፈላጊ መለዋወጫዎችን በማቅራብ ራስን በመቻል የጥገናና የእድሳት አገልግሎት በማድረግ በኪራይ ለማሽነሪዎች የሚወጣ ወጪን ሊያስቀር ይገባል፡፡

107.ኮርፖሬሽኑ በእርጅናና በተለያ ምክንያቶች ጥቅም ላይ የማይውሉ ቋሚ ንብረቶችን ባወጣው የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት እንዲወገዱ ሊያደርግ/ሊያስደርግ ይገባል፡፡

108.ኮርፖሬሽኑ የአካባቢ ጥበቃ እንክብካቤን በማስደረግ በተንዳሆ አብዛኛው ሰራተኛ የሚኖርበትን መንደር 18 በእፅዋት ወደ አረንጓዴነት እንዲቀየር በማድረግ ምቹ የመኖሪያ አካባቢ እንዲሆን ሊያስደርግ ይገባል፡፡